# የፖለቲካ ተግባቦት እና ምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ችሎታ የግንዛቤ ማዳበሪያ

## የሥልጠና መመሪያ

አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ
ጥር 2015 ዓ/ም

Funded by:
UKaid from the British people
Irish Aid Rialtas na hÉireann Government of Ireland
Embassy of Sweden Addis Abeba
Norwegian Ministry of Foreign Affairs

Managed by:
BRITISH COUNCIL
pact building local promise.
Social Development Direct

# የፖለቲካ ተግባቦት እና ምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ችሎታ የግንዛቤ ማዳበሪያ

# የሥልጠና መመሪያ

**ጥር 2015 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጲያ**

## Contents

**አጠቃላይ የማሠልጠኛ መመሪያው መግቢያ፡-** ..... iv

ክፍል አንድ ..... 1

1. የፖለቲካ ተግባቦት (Political Communication) ..... 1

1.1. ፖለቲካዊ ተግባቦት ምንድነው? ..... 1

መግቢያ፡- ..... 1

1.2. የፖለቲካ ተግባቦት ዋና ዋና ተዋናዮች ..... 6

1.3. ቴክኖሎጂን ማዕከል ያደረገ ፖለቲካዊ ተግባቦት ..... 9

1.4. የፖለቲካ ተግባቦት እውቀትን የሚወስኑ ዋና ዋና ምክንያቶች ..... 10

1.5. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ተግባቦት ዋና ዋና ተዋናዮች ..... 11

1.5.1. ሚዲያ ..... 12

1.5.2. ዕጩዎች ..... 13

1.5.3. የፖለቲካ አማካሪዎች ..... 15

1.5.4. የፖለቲካ ፓርቲዎች ..... 16

1.6. ፖለቲካዊ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ተግባቦት ..... 17

**ማጠቃለያ** ..... 20

ክፍል ሁለት ..... 21

2. መራጮችን የማሳመን ፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ ..... 21

መግቢ፡- ..... 21

2.1. ማሳመን (Persuasion) ምንድነው? ..... 22

2.2. ዕጩዎች መራጮችን የማሳመን ሂደቶች ..... 24

2.3. የማሳመን ብልሃቶች ..... 26

2.4. የፖለቲካ ትረካዊ የምርጫ ቅስቀሳ የማሳመን ስልት ..... 27

2.5. የፖለቲካዊ ተግባቦት የማሳመን አተገባበር ..... 28

2.5.1. ዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸው መራጮች የማሳመን አተገባበር ..... 30

2.5.2. ከፍተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸውን መራጮችን የማሳመን አተገባበር ..... 33

2.6. የምርጫ ቅስቀሳ የማሳመን ዘመቻ ዋና ዋና መንገዶች ..... 36

2.6.1. በዲጅታል ቴክኖሎጂ የተደገፋ የምርጫ ቅስቀሳ ..... 37

2.6.2. የፊት-ለፊት የምርጫ ቅስቀሳ ..... 37

2.6.3. ትዕይንተ ገፅታ የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ (The Panoply of Political Persuasion) ..... 38

2.7. ሴቶች እና የፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ ....... 42
ማጠቃለያ ....... 44
ክፍል ሦስት ....... 46
3. የኢትዮጵያ ምርጫ ቅስቃሳ ዘመቻ ህጋዊ ማዕቀፎች ....... 46
መግቢያ፡ ....... 46
3.1. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ አካሄድ (Rules of Election Campaign) ....... 47
3.2. ለምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ የተከለከሉ ሥፍራዎች ....... 49
3.3. በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሥለሚኖር ህጋዊ መስተጋብር ....... 50
4. ዋቢ መፀሐፍት (Referance Book) ....... 53

## አጠቃላይ የማሠልጠኛ መመሪያው መግቢያ፡-

ሴቶች በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈፃሚው፣ እንዲሁም በሕግ ተርጓሚው አካላት ውስጥ በብዛት እና በተመጣጣኝ ሁኔታ ካልተሳተፉ በማኅበረሰብ ውስጥ በዋነኛነት ቅድሚያ የምንሰጣቸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግቦችን ለማረጋገጥም ሆነ ለማሳካት የሚረዱንን አሳታፊ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ህዝባዊ አሰራርን ማምጣት አይቻልም። ይሁን እንጂ በሃገራችን እስካሁን በተካሄዱ ስድስት ተከታታይ የፖለቲካ ምርጫዎች ታሪክን መሰረት ተደረጎ፤ በተካሄዱ የጥናት ግኝቶች መሠረት ሴቶች በፖለቲካ መሪነት እና ውሳኔ ሰጪነት ያላቸው ተሳትፎ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ይህንን እውነታ ተከትሎ በሃገራችን ሴት ከፍተኛ አመራሮች ያሏቸው ፓርቲዎች ቁጥር አነስተኛ እንደሆኑ በዘርፉ ላይ የተደረጉ ጥናቶች በግልፅ ያመላክታሉ።

በተጨማሪም ሴቶች በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በተለይም በውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ላይ ያላቸው ውክልና ዝቅተኛ እንደሆነ በብዙ መንገድ ይገለፃል። ለዚህ ደግሞ ከበርካታ ምክንያቶች አንዱ ማህበረሰባችን ለሴቶች ባለው ኋላቀር ግምት፣ የፖለቲካ ስልጠና እና ትምህርት ዝግጅት ማነስ፣ ሴቶች ደካማ የሆነ የፖለቲካዊ ተግባቦት በማሳየታቸው ምክንያት በራስ መተማመናቸውን እንዲያጡ አድርጓቸዋል። ሴቶች በራሳቸው ሳይተማመኑ ደግሞ አደባባይ ወጥተው ፖለቲካን በድፍረት ለመምራት፣ በውሳኔ ስጭነት ለመሳተፍ፣ ለመናገር እና ለመከራከር እንዲሁም ሀሳባቸውን ለመግለጽ እንዲቸገሩ እንዳደረጋቸው የበርካታ ጥናት ውጤቶች ያረጋግጣሉ።

ከዚህ መሰረታዊ እውነታ በመነሳት ትምራን ከተመሰረተችበት ሴቶች በህዝባዊ እና ፖለቲካዊ አመራር ሠጭነት ላይ አቅም ማጎልበት ዓለማ አንፃር፤ ይህንን የስልጠና መመሪያ በማዘጋጀት ለሴት የፖለቲካ አመራሮች፣ የፖለቲካዊ ተግባቦት የአቅም ክፍተት ለመሙላትና የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ እና ህዝባዊ ውሳኔ ሠጭነት አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ማድረግና ማሻሻል ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል።

ይህ የሥልጠና መመሪያው የሴት የፖለቲካ አመራሮችን እና ውሳኔ ሠጭዎች የፖለቲካ ተግባቦትን አቅምና ችሎታን ለማሻሻል፤ ሴቶች ፖለቲካዊ የማሳመን ጥበብን እንዲካኑ እና ከምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ጋር ተያይዞ ሊነሱ የሚችሉ ህጋዊ ማዕቀፎችን በውል እንዲገነዘቡ ማስቻልን ያለመ ነው።

# ክፍል አንድ

## 1. የፖለቲካ ተግባቦት (Political Communication)

### 1.1. ፖለቲካዊ ተግባቦት ምነድነው?

መግቢያ፡-

በዚህ ክፍል ስለ ፖለቲካ ተግባቦት ምንነትና አተገባበር፤ በፖለቲካ ተግባቦት ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ተዋናዮችን፤ የፖለቲካ ተግባቦት እውቀትን የሚወስኑ ዋና ዋና ምክንያቶች እና የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ የሚሳተፉ ተዋናዮችን እንረዳለን፡፡ የፖለቲካ ተግባቦት ሠፊ የሆነ ፅንሰ ሃሳብ አለው፡፡ አጠር አድርጎ እንደመግቢያ ለመግለፅ ያህል ግን፣ ፖለቲካ ተግባቦት ማለት በቋንቋ እና ምልክቶች አማካኝነት በፖለቲካ መሪዎች፣ በመገናኛ ብዙኃን፣ በዜጎች፤ በመንግስት የስራ ሃላፊዎች፣ በግለሰቦች የፖለቲካ ግንዛቤ፣ የታሰቡ ወይም ያልታሰቡ ውጤቶችን በሠዎች አመለካከት እና ባህርይ ላይ ተፅእኖ ሊያመጡ የሚችሉ የፖለቲካ ሥራዓተ መልዕክቶች ናቸው፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ዋና ዋና ዓላማዎች**

**ሰልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የፖለቲካ ተግባቦት ምንነትና ትርጉም ያውቃሉ፤
- የፖለቲካ ምንነት በአጭሩ ይገነዘባሉ፤
- ዋና ዋና የፖለቲካ ተግባቦትን የሚወስኑ ምክንያቶችን ይረዳሉ፤
- የፖለቲካ ተግባቦት የቅስቀሳ ዘመቻ የዋና ዋና ተዋናዮችን ሚና ይገነዘባሉ፤

*የቡድን መወያያ ጥያቄዎች፡-*

ውድ ሠልጣኞች!

1. *ስለ ፖለቲካ ተግባቦት ከመወያየታችን በፊት ፖለቲካ ምንድን ነው?*
2. *አንድ ሰው ስለ ፖለቲካ ሲናገር ወደ አዕምሯችሁ የሚመጣው ምንድን ነው?*
3. *አንድ ዕጩ የፖለቲካ ተወዳዳሪ ለመራጮች ገለፃ ሲያደርግ  ምን ምን ጉዳዮችን ልታስቡ ትችላላችሁ?*
4. *እንደ ኢትዮጵያ ባለብዙ ብሄርና ቋንቋ ባለበት ሃገር ምን ዓይነት የፖለቲካ ተግባቦት ያሥፈልጋል ብላችሁ ታምናላችሁ?*

ፖለቲካ የሚለው ቃል በብዙዎች ዘንድ፣ በሁሉም አጋጣሚዎች ቃሉ በሰዎች አዕምሮ አሉታዊ ምስሎችን መከሰቱ የተለመደ ነው። ይህ በከፊል ፖለቲከኞች የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ አንዳንድ ሥነ ምግባር የጎደላቸው የፖለቲካ ስልትና ዘዴዎችን በመከተላቸው ምክንያት በሰዎች አዕምሮ ውስጥ አሉታዊ ምስሎችን ከስቷል፡፡ በተጨማሪም ዜጎች ብዙውን ጊዜ በፖለቲካ መሪዎች ላይ እምነት ስለሌላቸው እና የፖለቲካ ተግባቦት ማሰራጫዎች ደጋግመው ፖለቲካ በሕዝብ ሕይወት ውስጥ ያለውን ጥሩ ያልሆነ ጎን አግዝፈው ስለሚያሳዩ ነው።

ለአብነት ያህል የእኛን ሃገር ብንመለከት፣ ብዙዎቻችን ስለፖለቲካ ያለን ዕይታ "እገሌ ፖለቲከኛ ነው" ማለት ተንኮለኛ፣ ውሰጡ የማይገኝ፤ ክፉ፣ ሴረኛ ወዘተ……የመሳሰሉት አንድን ግለሰብ ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል እንደሆነ የሁላችንም ትውስታ ነው። እንዲሁም የአንድ የፖለቲካ አመራርን ወይም የፓርቲ ሹመኛን ንግግርን ቃላትና ሃረጋት ደጋግመን እያነሳን በጥሩም ሆነ በጉድለቱን ወይም መልካምነቱን ስንፈርጅ ጊዜ የምናባክነው ለዚሁ ነው።

እውነታው ግን ፖለቲካ ሳይንስ ነው። ፖለቲካ ህዝብንና ሃገርን የመምራት ጥበብም ነው። ያለ ፖለቲካ የተመሰረተ ሃገር የለም። በዘመናዊ ህዝባዊ አመራርና አስተዳዳር ጥበብ ውስጥ፣ ፖለቲካ የዲሞክራሲ ሥርዓት ወሳኙ አካል ነው። ያለ ፖለቲካ ዲሞክራሲ ሊኖርም አይችልም። በተጨማሪም ፖለቲካ አወንታዊ ለውጦችን ሊያመጣ እና የአንድ ሃገር ዜጎች ህይወት መሻሻልን ሊያመጣ የሚችል የአመራር ሳይንስ ነው። ፖለቲካ የአንድን ሃገር ሃብትና ስልጣን ማን፣ የትኛውን ሃብት እንደሚያገኝ እና ለምን ማግኘት እንዳለበት መወሰንን ጭምር ያካትታል።

ፖለቲካ ማለት ሂደት ሲሆን የግለሰቦች ስብስብ፣ አስተያየቶች ወይም ፍላጎቶች መጀመሪያ ላይ የተለያየ ሆኖ፣ ነገር ግን አንድን የጋራ ዓላማ እና ውሳኔ በጋራ ለማሳካት ሲሉ ቡድኖች የጋራ መግባባት የደረሱበት የራሱ የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ፖሊሲ፣ ማንፌስቶ፣ ስትራቴጂ ወዘተ....የመሳሰሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ሊኖረው የሚችል ህዝብን የማስተዳደር ሳይንስ ነው። ፖለቲካ እነዚህን የቡድን እና የጋራ ፖሊሲዎች በሃገር ደረጃ ተፈጻሚ ለማድረግ ግለሰቦች በጋራ ተደራጅተው፣ የጋራ ፖለቲካዊ ፍላጎታቸውን በአንድ ሃገር ተግባራዊ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱበት የአመራር ጥበብ ነው (Miller, 1987, p. 390)።

የፖለቲካ ተግባቦት ማለት ደግሞ በቋንቋ እና ምልክቶች  አማካኝነት በፖለቲካ መሪዎች፣ በመገናኛ ብዙኃን፣ በዜጎች፤ በመንግስት የስራ ሃላፊዎች፣ በግለሰቦች የፖለቲካ ግንዛቤ፣ የታሰቡ ወይም ያልታሰቡ ውጤቶችን በሰዎች አመለካከት እና ባህርይ ላይ ተፅእኖ ሊያመጡ የሚችሉ የፖለቲካ ሥርዓተ መልዕክቶች ናቸው።

በተጨማሪም የፖለቲካ ተግባቦት ማለት ፖለቲካ መሪዎች/ዕጩዎች እንዴት ከተከታዩቻቸው ወይም ከደጋፊዎች ጋር እንዴት፣ በምን ሊግባቡ እንደሚችሉ፣ ቋንቋ እና ምልክቶች የሚጫወቱትን ሚና እና የፖለቲካ መልዕክቶች በዜጎች፣ በፖለቲካ መሪዎች እና በትልቁ ህዝብ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ እና በአጠቃላይ  የፖለቲካ ሥርዓቱን መልዕክት የሚያጠና ነው።

በእርግጥ ፖለቲካዊ ተግባቦት ሂደት ነው።  ሂደት ነው ስንል አንድን ፖለቲካዊ  ውሳኔ ወይም ፖሊሲ ተረቆ እስኪፀድቅና ስራ ላይ እስኪውል ድረስ በርካታ በቀላሉ ማለቂያ የሌላቸው ፖለቲካዊ ንግግሮችና ውይይቶች አማካኝነት፣ ሰዎች የነበራቸውን አቋም ማስቀየር እና ለዛ ፖሊሲ ድግፋቸውን እንዲገልፁ ማስቀየርንም ስለሚያካትት ነው።

ለምሳሌ፡- የቀድሞው የአሜሪካ ፕሪዝዳንት አብርሃም ሊንከን ፖለቲካዊ ተግባቦት ለሃገራዊ እኩልነት እና አዎንታዊ ዓላማዎች ሊውል እንደሚችል ትክክለኛ የፖለቲካ ተግባቦት መንገዶቹን ለዓለም ህዝብ አሳይቷል። ሊንከን ሌሎችን ለማሳመን የፖለቲካዊ የተግባቦት ረዥም ሂደቶች እና ስልቶች በአግባቡ ተጠቅሟል፡፡ ይህም ኮንግረሱን የአስራ ሦስተኛውን ማሻሻያ ውሳኔ በሰፊ የፖለቲካ ክርክር እና ውይይት በማሳለፍ፣ የጥቁር አሜሪካውያን ዜጎችን ባርነት የሚፈቅደውን ህግ ከአሜሪካ የአስተዳዳር ታሪክ መሰረዝ ችሏል። ይህም ረዥም ፖለቲካዊ ተግባቦት ሂደት ለመልካም ተፅኖ በማዋል የሰዎችን እኩልነት በህግ ፊት ማረጋገጥ ችሏል ማለት ነው፡፡

ሌላው ጉዳይ በፖለቲካ ተግባቦት ውስጥ ቋንቋ እና የምልክቶች አጠቃቀም ትልቅ የሆነ ተፅእኖ አለው። ምልክት አንድ አካል ሀሳቡን ወይም ሥራዓተ-መልዕክቱን የሚወክልበት ነው። ለምሳሌ ፡-ሰዎች ፍትህን ለመግለፅ የሚዛንን ወይም ምልክትን ሲጠቀሙ፤ የሠላም ምኞታቸውን ወይም ፍላጎታቸውን ደግሞ የእርግብን ምሰልን ወይም ምልክትን የጠቀማሉ፡፡

የፖለቲካዊ ተግባቦታችን ከፍተኛ የሰዎችን ስሜት እና ወኔ ወደ መልካም የሆኑ የሰዎች የጋራ ጉዳዮች የሚቀሰቅሱ፣ የመጭውን ጊዜ ብሩህ ተስፋን የሚሰንቁ ቃላትና መልዕክቶችን ያካተተ፣ እና መልዕክቶቹ የሚያስተላልፉት ትርጉም የተለያዩ ቡድኖች እና ነፃነት እኩልነት ያካተተ ሊሆን ይገባል።

*ውድ ሠልጣኞች!*

*የሃገራችን ፖለቲከኞች በአደባባይ እና በብዙኃን መገናኛዎች ለሚያደርጉት ንግግር ምን ያህል ጥንቃቄ ያደርጋሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? በአዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደሩባችሁን ንግግሮችን በምሳሌ በማስረዳት በቡድን ተወያዩባቸው፡፡ ጉድለታቸውና ጥንካሪያቸውን ገምግሙ፡፡*

በተለይ እንደ እኛ ሃገር ባለ ብዙ ብሄርና ቋንቋ ህዝብ ባለበት ሃገር በተቻለ መጠን የምናስተላልፋቸው ፖለቲካዊ መልዕክቶች ህዝብን ማዕከል ያድረገ ሊሆን ይገባል። የፖለቲካ ተግባቦት ዋና ዓላማ ምክንያታዊ እና እውነታዊ በሆነ መንግድ የሰዎችን አቋምና አስተሳሳብ የሚያስቀይር ወይም ዜጎችን በአስተሳሰባቸው ከተናጋሪው የፖለቲካ ፕሮግራም ጎን እንዲሠለፉ ነው። ምክንያቱም ከፋፋይ መልዕክት ከሆነ ግን ሰዎች በተላለፈው ከፋፋይ መልዕክት ጥርጣሬ ስለሚገባቸው ከመልዕክት አስተላላፊው የፖለቲካ ዓላማ ጎን ላይሰለፉ ይችላሉ።

የፖለቲካ ተግባቦት በርካታ ጉዳዩችን አካትቶ ይይዛል። የአንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ፕሬዝዳንታዊ የምርጫ ዘመቻ ክርክሮች እና የህዝብ ትኩረት የሚስቡ መልዕክቶች ማስተላፍን፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ፖለቲካ እስከ ሌሎች አካባቢያዊ እና ዓለማቀፋዊ የሰላምና ደህንነት ባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የዜጎችን አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የተነደፉ ዘመቻዎች እና ህዝባዊ ቅስቀሳን አካትቶ ይይዛል። ሌሎች ድብቅ የፖለቲካ ዓላማዎችን ለማሳካት በሰዎች አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የተነደፉ ልዩ ልዩ ዘመቻዎችንም ይጨምራል።

ልክ እንደ ሁሉም የዓለማችን የፖለቲካ ተፅዕኖ መፍጠርያ መንግዶች ሁሉ፣ የሰዎች ፖለቲካዊ ተግባቦት በራሱ ለአዎንታዊ እና አሉታዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። በፖለቲካዊ ተግባቦት ግርማ ሞገስ ያላቸው ተናጋሪዎች ሰዎችን ወደ የጋራ ወደ ሆነ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ርህራሄ እና ተስፋ ሊያንቀሳቅሡ ይችላሉ። ልክ እንደ የማርቲን ሉተር ኪንግ፣ የሮበርት ኦፍ ኬኔዲ፣ የሮናልድ ሬጋን እና የኔልሰን ማንዴላ ንግግሮችን የሰሙ ለዚህ ትልቅ ማረጋገጫ ናቸው። በመሆኑም ግለሰቦች በፖለቲካ ተግባቦታቸው ሰዎችን ለአንድ ለጋራ ጥቅም እንዲተባበሩ ሲያንቀሳቅስ ለሃገር ግንባታ ትልቅ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ነገር ግን በአሉታዊ ፖለቲካዊ ተግባቦታቸው ደግሞ በጭፍን ጥላቻ፣ የከረረ ዘረኝነትን በመስበክ ሰዎችን ወደ አላስፈላጊ ወደ ሆነ እልቂትና እርስበርስ መጠራጠር በመውሰድ በሰዎች መካከል ጦርነት እንዲፈጠር ሊያደረጉ ይችላሉ። እ.ኤ.አ. በ1930ዎቹ የጀርመኑ ሂትለር፣ የ1990ዎቹ የሩዋንዳውን የዘር ፍጅት እና የኦሳማ ቢንላደን ንግግሮች በራሳችን ክፍለ ዘመን አሉታዊ ፖለቲካዊ ተግባቦቶች ምሳሌዎች ናቸው። ፖለቲከኞች በንግግራቸው የማጭበርበር እና ማታለል ዘዴዎችን ተጠቅመው የዜጎችን ስሜት ሲጎዱ በህግና በሥነ ምግባር ተጠያቂነትን ሊያመጣ ይችላል።

የፖለቲካ ተግባቦት የመልካም እና የክፋት ኃይል ሊሆን ይችላል:: ልክ እንደ ሁሉም የተፅዕኖ መፍጠሪያ መሳሪያዎች ሁሉ የፖለቲካ ተግባቦት ለአዎንታዊ እና አሉታዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል:: የሰው ጭፍን ጥላቻ መራራቅን፣ ዘረኝነትን፣ መከፋፈልን ወዘተ.. ላይ የሚያተኩሩ ፖለቲካዊ ተግባቦቶች በዜጎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያመጣሉ:: በተቃራኒው ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው ፖለቲካዊ ተግባቦቶች አንድነትን፣ ፍትህን፣ መተሳሰብን፣ እኩልነትን የሚሰብኩ ከሆነ ለሃገር ግንባታ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የፖለቲካ ተግባቦት ሃይል በብዙዎች ብሩህ የሆነን ተስፋ በውስጣቸው እንዲያንሰራራ ሊያደርግ ይችላል:: ለዚህ ነው አበው ‹‹…ቃል፣ ያድናል፣ቃል ይገድላል..›› የሚሉት፡፡ ለዚህ ነው አርስቶትል ‹‹ጥሩ ህይወት ንቁ የሆነ ፖለቲካዊ ተግባቦትና ተሳትፎን ያካትታል፡፡ ይህም በጋራ የፖለቲካ ተግባራት ላይ ከሌሎች የጋር የሆነ ተግባቦት መፍጠር ነው›› በማለት ፖለቲካዊ ተግባቦትና ንቁ ተሳትፎን በማስተሳሰር ያብራራው፡፡

በአጠቃላይ የእኛ ኢትዮጵያዊያን በኢፌዲሪ ህገ መንግስታችን ከተረጋገጡት የዴሞክራሲ እና የሰብአዊ መብቶች አንዱ እና ትልቁ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ነው፡፡ ነገር ግን የተግባቦት ባህላችን የበለጠ አድማጭ እንድንሆን አድርጎ እንደቀረፀን፣ የአንዳንድ ጥናት ውጤቶች በትኩረት ይገልፃሉ:: በተለይ ሴቶች ላይ የተግባቦት ሥነ-ምግባራችን/ባህላችን ሃሳባችንን በግልጽ ከማሰማት ይልቅ፣ የአንድን ተናጋሪ የመደመጥ እድል አብላጫውን ድርሻ እንዲኖረው ቅድሚያ ይሰጣል:: በዋነኝነት ሴቶች ወላጆቻቸው ከማውራት ይልቅ ሌሎች ሲናገሩ በጥሞና እንዲያዳምጡ አድርገው እንዲያሳድጓቸው ባህላችን ያስገድዳል::

## 1.2. የፖለቲካ ተግባቦት ዋና ዋና ተዋናዮች

ተግባቦት የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት በፖለቲከኞችና ፖለቲካው ውስጥ ባሉ ተዋናዮች የሚዘጋጅ የፖለቲካ ማስታወቂያን ጨምሮ በየመድረኩ የሚደረጉ ንግግሮችን ያካትታል፡፡ በመጀመሪያ በግለሰቦች፣ ቀጥሎም ተመሳሳይ ሐሳብ ባላቸው ሰዎች አስተሳሰብና ባሕርይ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ በአዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊመዘን ይችላል፡፡

ፖለቲካዊ ተግባቦት በዋነኝነት ሶስት ዋና ዋና ፈፃሚ ተዋናዮችን አካቶ ይይዛል፡፡ እነሱም ዜጎች፣ የፖለቲካ ልሂቃን እና ሚዲያዎች ናቸው፡፡ የአንድ ሃገር ፖለቲካ ጤናማነት እና ለሃገር

ያለው ፋይዳ በነዚህ ዋና ዋና ተዋናይ አካላት ፖለቲካዊ ተግባቦት መስተጋብር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

ከነዚህ ተዋናዮች ውስጥ አንደኛው የፖለቲካ ልሂቃን (poitical Elite) ናቸው፡፡ በፖለቲካ ልሂቃን ውስጥ ከሚካተቱት ውስጥ ደግሞ የተመረጡ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የፕሬዚዳንቱ/ቷ ወይም የጠቅላይ ሚኒስትሩ/ሯ እና የካቢኔ አባላት፣ የፖሊሲ ባለሙያዎች፤ ተቃዋሚዎች እና በሰፊው መንግሥት ውስጥ ያሉ ሹማምንት እና ሌሎቸንም አካቶ ይይዛል፡፡ ዴሞክራሲ በሊቃውንት ቡድኖች ወይም ተፅዕኖ ፈጣሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ውድድርን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ነው፡፡ ዴሞክራሲ ዜጎች በተለያዩ ልሂቃን የመወከል እድላቸውን በመጠቀም ብቻ ዲሞክራሲዊ ተግባራቸውን መወጣት እንደሚችሉ ያስገነዝባል፡፡ ልሂቃን የፖለቲካ ስልጣን በያዙ መሪዎች ላይ ተፅእኖ በመፍጠር እና ህፀፆችን/ጉድለቶችን በማሳየት ምን አልባትም የፖለቲካ ሥልጣንን ሊቆጣጠሩ የሚችሉ ተደማጭነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍል ናቸው፡፡

የፖለቲካ ተግባቦት ተዋናይ ከሆኑት አካላት ውሰጥ ቀጥለን የምንመለከታቸው ሚዲያዎች ናቸው፡፡ ሚዲያዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያየ ቡድኖችን ያካትታሉ፡፡ የተለመዱ የዜና ሚዲያዎች፣ ብሎገሮች፣ የሞባይል ካሜራ የታጠቁ ሰዎች እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ራሳቸውን የዜጋ-ጋዜጠኞች ብለው የሚጠሩ፣ የድረ-ገጾች ከፊል አራማጆች እና የፖለቲካ መዝናኛ አስተናጋጆች እና ኮሜዲያኖችን አካቶ ይይዛል፡፡

መገናኛ ብዙኃን የፖለቲካ ተግባቦት የመድረሻ ቀዳሚ ነጥቦቻችን እና የሚቀድሙት የሚዘግቡ፤ የሚቀርጹ እና አንዳንድ ጊዜም የተጨማሪ አካላትን ተሳትፎ የሚወስኑ ናቸው፡፡ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ግጥሚያዎች ዋነኛ ቁልፍ ተዋናዮች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሚዲያዎች የሚቀርቡበት መንገድ እና ዓይነት በብዙ ቅርጾች ይይዛል፡፡ በመጻፍት፣ በመጽሔቶች፣ በጋዜጦች፣ ማስታወቂያዎች፣ ቀጥታ መልዕክት፣ ሬዲዮ፣ ፊልም፣ ኢሜይሎች፣ ድረ-ገጾች፣ ብሎጎች፣ ማህበራዊ ድረ-ገጾች፤ በኬብል እና በኔትወርክ ቴሌቪዥን ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም ብዙ ልብለድ እና ልብለድ ያልሆኑ ዘውጎችን አካትቶ ይይዛል፡፡ ሚዲያዎች ስለ ፖለቲካዊ ሀሳቦች፣ ጉዳዮች፣ ክስተቶች ወይም ተዋናዮች መረጃን ለታዳሚው ያደርሳሉ፡፡ ከእኛ ቀጥታ የዘወትር ልምዳችን ውጪ የእኛን የፖለቲካ ዓለም አዕምሯዊ ካርታዎችን ምስል ይከስታሉ፡፡ በአሁኑ

ጊዜ ሚዲያ ሳንጠራ ስለ ፖለቲካ ስኬት ፈፅሞ ማውራት አንችልም፡፡ ምክንያቱም ሚዲያዎች በዘመነ ዲጅታል ዓለም ውስጥ ፖለቲካዊ ስኬትን ለመጎናጸፍ ከፍተኛ ሚና ሥላላቸው ነው፡፡

ሌላኛዎቹ የፖለቲካ ተግባቦት ማዕከል ዜጎች ናቸው፡፡ ዜጎች ፖለቲካ በንቃት የሚከታተሉ እና አስተያየት ሰጪዎች ወይም በግድየለሽ የፖለቲካ አላዋቂነት የተጠመዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ዜጎች ስንል በሲቪክ ቡድኖች ውስጥ በንቃት የሚሳተፉትን ያጠቃልላል፡፡




*ምስል-1. ዋና ዋና የፖለቲካ ተግባቦት ፈፃሚ ተዋናዮች*

በአጠቃላይ የአንድ ሃገር የፖለቲካ አውዶች ሦስቱም ዋና ዋና ተዋናዩች ጋራ መስተጋብር ይወሠናል፡፡ ፖለቲካ ልሂቃን፣ ሚዲያ እና የዜጎች በጋራ  ውስብስብ በሆነ መንገድ መስተጋብር ይፈጥራል፡፡

## 1.3. ቴክኖሎጂን ማዕከል ያደረገ ፖለቲካዊ ተግባቦት

በዚህ በዘመነ ሉላዊነት ጊዜ ቴክኖሎጂ አንዱ የፖለቲካ ተግባቦት ማዕከል ነው። ምንም እንኳን ቴክኖሎጂ ሁልጊዜ በፖለቲካ ተግባቦት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ቢመጣም፣ በአሁኑ ሰዓት ግን ብንፈልግም፣ ባንፈልግም በእለት ከዕለት ህይወታችን ውስጥ ፖለቲካዊ ተፅዕኖው በእጅጉ እየጎላ መጥቷል። ቴክኖለጂው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው መረጃ በማሠራጨት፣ የበለጠ ፈጣን ግንኙነት በማስፋት፣ በፖለቲካ መሪዎች፣ በዕጩ ተከታዮች መካከል እና መራጮች ትክክለኛ መሪያቸውን የሚለዩበትን ተጨማሪ እድሎች በር ከፍቷል።

አሁን አሁን የምርጫ ቅስቀሳ እና ዘመቻዎች በቴሌቭዥንና ሬዲዮ አውታሮች ብቻ ማከናወን ውጤታማ ላያደርግና እየተተወ የመጣ ይመስላል። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ፖለቲከኞች በማህበራዊ ድህረ-ገጾች ላይ ትልቅ ተሳትፎ ከማድረጋቸው በተጨማሪ መልዕክቶቻቸውን እና የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ለህዝብ በማህበራዊ ድህረገፆች ያስተላልፋሉ። የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ እና የተፎካካሪ ፓርቲ ቡድን ጥቃት ማስታወቂያዎች በፍጥነት በዩቲዩብና በልዩ ልዩ ማህበራዊ ገፆች ላይ ይለቀቃሉ። ይህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ተደራሽ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል።

በፖለቲካ ቅስቀሳ እና ዘመቻ ወቅት ማህበራዊ ሚዲያዎች ትልቅ የሆነ ጠቃሚ ሚና ተጫውተዋል፤ ወደፊትም ሚናቸው የጉላ ነው። በዚህ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የመረጃዎች ፍጥነት፣ በደቂቃና ምንአልባትም በሰከንድ ውስጥ በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ስትራቴጂካዊ ለውጦች ላይ ፖለቲካኞች ትዊት ወይም ፖስት ያደርጋሉ። እንዲሁም በቀን ውስጥ በተደጋጋሚ የፖለቲካ ማስታወቂያዎችን ይለቀቃሉ።

*ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2012 የአሜሪካ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ የቀድሞው የአሜሪካው ፕሬዝንት ኦባማ የምርጫ ቅስቀሳቸውን ከተለመደው የመገናኛ ብዙኃን ስልት ወጣ በማለት የህዝባቸውን ድምፅ እና ድጋፍ ለማግኘት ከዜና ጣቢያ ወደ ዘመኑ ቴክኖሎጅካል ተግባቦት ማህበራዊ ሚዲያን ፊታቸውን አዙረው ነበር። በማህበራዊ ሚዲያ እንዲህ በማለት፡-*

*‹‹ውድ! ወጣት መራጮች ሰላም፣ እኔ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ነኝ። ማንኛውም ጥያቄ ጠይቁኝ›› በማለት የዘመኑን የሚዲያ ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ለደጋፊዎቻቸውና ለመራጮች ምን ያህል ቅርብ መሆናቸውን አሳይተዋል።*

*በአጠቃላይ ዘመኑን የዋጀ፣ ዘመናዊ ዲጂታል-ቴክኖሎጂን የተላበሰ የፖለቲካ ተግባቦት፣ ለፖለቲካ ስኬታችን ጉልህ የሆነ ድርሻ እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል።*

## 1.4. የፖለቲካ ተግባቦት እውቀትን የሚወስኑ ዋና ዋና ምክንያቶች

ቀጥሎ በፖለቲካ ተግባቦት ውስጥ የፖለቲካ ዕውቀትን የሚወስኑ ዋና ዋና ጉዳዩች ቀርበዋል። እናንተ ድግሞ እያንዳንዱ ምን ማለት እንደሆነ በጋራ ከአሰልጣኞችሁ ጋር በጋራ እየተወያያችሁ አዳብሯቸው።

1. የስነ-ሕዝብ አወቃቀር ምክንያቶች

- ትምህርት
- ገቢ
- ዕድሜ

2. የስነ-ልቦና ሂደቶች

    - የግንዛቤ ችሎታዎች
    - የእውቀት (cognitive) መርሃ-ግብሮች

3. የፖለቲካ ሚዲያ አጠቃቀም

    - ጋዜጦች
    - ስርጭት እና የኬብል ዜና
    - የዜና ፕሮግራሞች
    - የምሽት ኮሜዲዎች
    - የኢንተርኔት ብሎጎች

4. የፖለቲካ እውቀት

- የሥነ ዜጋ ትምህርት
- የውጭ ጉዳዮችን በንቃት የመከታተል፣
- የሃገር ውስጥ ጉዳዮችን በንቃት የመከታተል፣

## 1.5. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ተግባቦት ዋና ዋና ተዋናዮች

**ውድ ሠልጣኞች!**

*በፖለቲካ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች ውስጥ ዋና ዋና ተዋናዩች እነማን ናቸው? ምንስ ይከውናሉ?*

ይህ ክፍል በምርጫ ዘመቻ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ተዋናዮችን ዝርዝር ተግባራቸውን ያብራራል። የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች በዘመናዊው ዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ የሆነ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች የአንድን ሃገር ውሳኔ ሰጪ መሪዎች እንዲመረጡ፣ ለሃገር ጠቃሚ የሆኑ ፖሊሲዎች ለህዝብ ይፋ እንዲሆኑ፣ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር እንዲኖር፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲአቸውን እና የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን በክርክር እና በማህበራዊ ቦታዎችን እያቀረቡ በህዝብ እንዲያጸድቁ ሠፊ አስተዋፆ አላቸው።

በፓርቲዎች መካከል የሚደረጉ ክርክሮች ትልቅ የሆነ የሃሳብ ግጭቶች የሚንፀባረቁበት ህዝባዊ መድረኮች ናቸው። ህጋዊ፣ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እና የፖለቲካ መሪዎችን፣ መራጮችን እና እጩዎችን አንድ በማድረግ የዜግነት ሃላፊነታቸውን እና የብሔራዊ ሃገራዊ መታደስ ሥነ-ሥርዓቶችን እንዲካሄዱ ትልቅ የሆነ በር ይከፍታሉ። በአጭር አነጋገር የፖለቲካ የምርጫ

ቅስቀሳ ዘመቻዎች የዴሞክራሲን ዓላማ እና ግብ ያሳካሉ፡፡ ይህም ዜጎች የወደፊት መሪዎቻቸውን ለመወሰን ዕድል ይሰጣል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ቁልፍ የሆነ ሚና አላቸው፡፡ እጩዎች የፖሊሲ አማራጫቸውን ለመራጩ ህዝብ ይፋ የሚያደርጉበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ በልዩ ልዩ ሁኔታ ዜጎችን እና ዕጩ መሪዎችን በክርክር፣ በመደማመጥ እና በውይይት አንድ መድረክ ላይ ያሰባስባሉ፡፡

በዚህ መሠረትም የፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ በርካታ ተዋናዮች አሉ፡፡ ቀጥሎ ዋና ዋናዎቹን አንድ በአንድ እንመለከታለን፡፡

### 1.5.1. ሚዲያ

ሚዲያ ለሁለት ዓይነት ተግባራት እንደሚያገለግል እናስታውስ፡፡ የመጀመሪያው በፖለቲካ እጩዎች እና በዜጎች መካከል የመገናኛ ድልድይ በመሆን የሚያገለግል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ዕጩዎች የሚያቀርቡትን የፖለቲካ ፕሮግራም እና የፖሊሲ አማራጮች ለመራጩ ህዝብ በማስተላለፍ ሠፊ ጠቀሜታ አለው፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ የሚያቀርቧቸው የፖለቲካ ፕሮግራሞች እና ሃሳቦች በጋዜጠኞች አማካኝነት ይተረጎማሉ፣ ይብራራሉ፣ ይተነተናሉ እንዲሁም ይሞገታሉ፡፡ ተንታኞች እና ብሎገሮች በዜና ታሪኮች፣ ንግግሮች፣ አስተያየቶች እና በትዊተር አማካኝነት ብዙ መልዕክቶችን እና ሃሳቦች ያስተዋውቃሉ፡፡ ሚዲያዎች በፖለቲካ መሪዎች እና በዜጎች መካከል አማካኝ ድልድይ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ የሚካሄድበት ሠፊ የመጫወቻ ሜዳም ጭምር ናቸው (ጆንስ፣ 2010፣ ገጽ 23)፡፡ ሚዲያዎች የፖለቲካ ነፃ የሃሳብ ግጭቶች የሚካሄድባቸው፣ የሃሳብ ልዕልና የሚንፀባረቅበት የክርክር እና የውይይት መድረኮችም ጭምር ናቸው፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎችን በሚዲያዎች የየራሳቸውን ገፅታና ምስል ፖሊሲና አማራጭ በማቅረብ፣ አንዱ ከሌላው የተሻለ አማራጭ እንዳለው ወይም

ሌላውን በማጣጣል የሚደረገውን ሠላማዊ ክርክር ለመራጩ ህዝብ መረጃን ያስተላልፋሉ፡፡ እጩዎች እይታን የሚስቡ ምስሎችን ለማስተላለፍ ሲሞክሩ፣ ጋዜጠኞች በእጩዎች ገፅታ ላይ የራሳቸውን ቅርፅ እና ይዘት ይዘው ይቀርባሉ፡፡ ይህ ማለት ጋዜጠኞች ዕጩው/ዋ በመደገፍ፤በማጣጣል ወይም ትክክለኛውን መረጃ ለህዝብ በማቅርብ የተለያየ አሰሣላለፍ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ መራጮች ደግሞ በእጩዎች የፖሊሲ ማዕቀፍ አቀራረብ፣ በጋዜጠኞች ዜና ሽፋን እና ራሳቸው ባላቸው አቋም ተመስርተው መጨረሻ ላይ ድምፅ ይሠጣሉ፡፡

በዲሞክራሲው ሥርዓት ውስጥ በተሻለ መልኩ ተራምደዋል የሚባሉ የምዕራባውያን ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከፈላቸው የግል ሚዲያዎች ሃገራዊ በሆኑ የምርጫ ቅስቀሳ ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ነገር ግን በዝቅተኛ ደረጃ በሚደረጉ የምርጫ ውድድሮች ልክ እንደ አካባቢያዊ የምርጫ ውድድሮች፣ የግዛት ውድድሮች እና አንዳንድ የምክር ቤት ውድድር እጩዎች ሁልጊዜ የቴሌቪዥን የአየር ሰዓት ማስታወቂያዎችን ለመግዛት በጀት ስለማይኖራቸው በብዛት ሲጠቀሙ አይስተዋልም፡፡ በዚህም የተነሳ በመገናኛ ብዙሃን ውስጥ ጥሩ የዜና ሽፋኖችን ለማግኘት ይጥራሉ፣ ዕጩዎቻቸውን በድህረ-ገፅ እና በማህበራዊ ሚዲያ ተጠቅመው ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ፤ በአካባቢያዊ ምርጫዎች ድምጽ ለማግኘት የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን ያሠማራሉ፣ በዲጂታል ሚዲያ የተጠናከረ ጨኸት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎችን ያደርጋሉ፡፡ ሥለሆነም ዝቅተኛ ደረጃ የአካባቢ ምርጫዎች ውስጥ ዲጂታል ሚዲያን መጠቀም ትልቅ ሚና ሊጫወት ይችላል ማለት ነው፡፡

## 1.5.2. ዕጩዎች

ለማንኛውም የስልጣን እርከን የሚደረግ የፖለቲካ ምርጫ ውድድርን በተመለከተ የሪቻርድ ቤን ክሬመርን የተባለ ፀሃፊ ሰፊ መጽሐፍ ለአንባቢ አበርክቷል፡፡ በጽሁፋም ሥለዕጩዎች እንዲህ በማለት አብራርቷል፡፡

<u>ውስን ጥናት (Case Study)</u>

*አሁን ለፖለቲካ ዕጩዎች የሚያስፈልገው ወደ ሥልጣን የሚወስደው ትክክለኛ መንገድ ብቻ ነው፡፡ "ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የህዝብ ተወካዩች ም/ቤት፣ የግዛት አስተዳዳሪ ለመሆን መመኘት ብቻ ሳይሆን ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን እየተራመድኩኝ ነው" የሚል መንፈስ በውስጣቸው ማዳበር አለባቸው "ዕጩዎች ራሳቸውን ከፍ አድርገው መመልትና ራሳቸውን ታሪክ ሠሪ አድርገው ማሰብ መጀመር አለባቸው" (Cramer,1992, p. viii)፡፡*

*<u>የቡድን መወያያ ጥያቄዎች</u>*

1. *እናንተ ዕጩ ተወዳዳሪ ብትሆኑ በየትኛው የሪቻርድ ቤን ሃሳብ ትስማማላችሁ? በየትኛው የሪቻርድ ቤን ሃሳብስ አትስማሙም ለምን?*
2. *እናንተ ከዚህ በፊት ባላችሁ ቅድመ ግንዛቤ ዕጩ የፖለቲካ ተወዳዳሪዎች ሊላበሷቸው የሚገቡ ባህሪያት ምን ምን ሊሆኑ ይገባል ትላላችሁ?*

ዕጩዎችም ትልቅ እምነት የሚጣልባቸው፣ ሠፋ ያለ የፖለቲካ እይታን ያካበቱ፣ የሀገር ፍቅርን በውስጣቸው የሰነቁ እና የሃገርን ፖለቲካዊ ሂደት ዳራ በውል የተረዱ፣ አንደበተ ርቱዕ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ዕጩዎች ምናልባትም ከታላላቅ የወደፊት የፖለቲካ ዓላማዎች ስኬት ከፍተኛ የስነ-ልቦና ሽልማቶችን የሚያገኙ፣ ሌሎችን በሚረዱና ሊረዳ የሚችል እና ከራስ በላይ በሆኑ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ማምጣት የሚሹ ሊሆኑ ይገባል (ስቶን፣ 2010)፡፡ በመራጮች እይታ ጥሩ እጩዎች የሚከተሉትን ባህሪያት ያሳያሉ፡፡ ቅንነት፣ ሐቀኝነትን፣ ርህራሄን እና ስለ ዋና ዋና ሃገራዊ ጉዳዮች ለመናገር እና ለመተግበር ዝግጁነት፣ ቁርጠኝነትን መላበሳቸውን ይገልፃሉ፡፡

## 1.5.3. የፖለቲካ አማካሪዎች

ውድ ሰልጣኞች!

*የፖለቲካ አማካሪዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ምን ተግባራትን ያከውናሉ ብላችሁ ታሰባላችሁ?*

የፖለቲካ አማካሪዎች የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችን ክፍተት እና የስራ ጫና በመቀነስ በፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በእርግጥ እንዲህ አይነት አሰራር በሃገራችን በተደረጉ ተከታታይ ምርጫዎች ታሪክ እምብዛም የተለመደ አይደለም፡፡ የፖለቲካ አማካሪዎች የምርጫ ቅስቃሳ ዘመቻዎች ፈፃሚ ተዋናዮች ናቸው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት ቁጥር እየቀነሱ ሲሄዱ እና የፓርቲ መሪዎች በዘመቻ አስተዳደር ውስጥ አነስተኛ ሚና ሲጫወቱ፣ አማካሪዎች ክፍተቱን በመሙላት ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ በጎ ፈቃደኞችን ለማደራጀት እና ዘመቻዎችን ለማካሄድ በፓርቲዎች ላይ ብቻ ጥገኛ መሆን በቂ ስላልሆነ፣ እጩዎች ወደ አማካሪዎች ፊታቸውን ማዞር ለፖለቲካ ስኬት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ እናም አማካሪዎች የፓርቲዎች የመገናኛ ብዙኃን ዘመቻዎችን በማሳለጥ ረገድ ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ ዕጩዎች ስለ አማካሪዎች ሲያስቡ፣ ትልቅ የፖለቲካ ስኬቱን አብረው ሊያስታውሱ ይገባል፡፡

የፖለቲካ አማካሪዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት፣ የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲን ሃይል አሠላለፍ ያጠናሉ፡፡ የዘመቻ ስልቶችን ያዘጋጃሉ፣ ምርጫዎችን ያካሂዳሉ፣ የምርጫ ቅስቀሳ መልዕክቶችን ያዘጋጃሉ፡፡ በመገናኛ ብዙኃን ላይ ያተኮሩ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ቅስቀሳና ዘመቻ እንዲሁም በግለሰቦች መካከል ቀጥታ ውይይት እና ክርክር ምላሽ መስጠት እና በመስመር ላይ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚሰጡ ምላሾችን ይቆጣጠራሉ፡፡ አማካሪዎች በተለምዶ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ በአንዱ ወይም በብዙ ላይ ሊሠማሩ ይችላሉ፡፡ የፖለቲካ አማካሪዎች ሥራቸው ጥበባዊ ወይም ሳይንሳዊ እና ከፍተኛ እስታስቲካዊ ሊሆን ይችላል (Johnson፣ 2000)፡፡

አማካሪዎች በዋነኝነት የሚመሩት በአንድ ግብ ነው። እሱም ምርጫውን በድል እና በአሸናፊነት ማጠናቀቅ ነው። በፖለቲካዊ ፉክክር ውስጥ ማሸነፍ ሁሉም ነገር የመጨረሻ ግብ ነው። ሌላ ጥሩ ሁለተኛ ቦታ የለም። ሌላ ተጨማሪም  የሁለተኛ ደረጃ ሽልማት የለም በቃ ማሸነፍ!…ማሸነፍ እና ማሸነፍ ነው።

### 1.5.4. የፖለቲካ ፓርቲዎች

የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀት እና ቁጥር እንደ ሃገሮች የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ታሪክ እና ህገ-መንግስት ይለያያል። የእኛ ሃገር ህገመንግስት ባለብዙ ፖለቲካ ፓርቲ ስርዓትን (Multi Party System) የሚፈቅድ ሲሆን ይህንን ተከትሎም ዛሬ በሃገራችን ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎ እንዲኖር አስችሏል።

ከዚህ በተቃራኒው ድግሞ አሜሪካኖቹ ሁለት ተፅእኖ ፈጣሪ የሆኑ ሃገራዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ማለትም ሪፐብሊካንና ዲሞክራት የሚባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመላ ሃገሪቱ የየራሳቸውን የተለያየ ርዕዮተ-ዓለምን በማራመድ ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው እና ጉልህ ሚናቸው ገዝፎ ወጥቷል ማለት ነው። ይሁንጂ ሌሎች ለነዚህ ፓርቲዎች አስተዋፆ የሚያበረክቱ በየአካባቢው/ግዛቶች ውስጥ ትንንሽ ፓርቲዎች የሉም ማለት ግን አይደለም። በተጨማሪም ሁለቱ አውራ ፓርቲዎች ሁልጊዜ ተመሳሳይ እና ቋሚ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም እና የፖለቲካ ፕሮግራም ዓላማ ይኖራቸዋል ማለትም አይደለም።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቁና ንቁ ዕጩዎችን ለምረጡኝ ቅስቀሳ በማቅረብ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻቸውን ያከናውናሉ። ፓርቲዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት በሥነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ፤ አንደበተ-ርቱዕ የሆኑ፣ በህበረተሰቡ ቅቡልነት ያላቸው፤ በፖለቲካዊ ብስለታቸው የተሻሉ፤ በተቻለ መጠን ጥሩ የስራ እና የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቢያቀረቡ አሸናፊነታቸውን ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል የበርካታ የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ። ምንም እንኳን በፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲው ሚና ከግለሰብ ዕጩው/ዋ የበለጠ ጉልህ አስተዋፆ ያለው ቢሆንም፣ የሚቀርቡ ዕጩዎች ግለሠባዊ ሚና የሚናቅ አይደለም።




ምስል-2. *የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ዋና ዋና ተዋናዮች*

## 1.6. *ፖለቲካዊ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ተግባቦት*

የምርጫ ቅስቀሳ አማራጭ ፖሊሲዎችን እና ለሃገራዊና አካባቢዊ ፖለቲካዊ ችግሮች ፖለቲካዊ የመፍትሄ አቅርቦ የመራጮችን ትኩረት ለመሳብና የፖለቲካ ፕሮግራምን ለመራጩ ህዝብ ለማስተዋወቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ይህም ከምርጫው ወሳኝ ክፍል መካከል አንደኛው ነው፡፡ በዲሞክራሲ ምህዳር ፖለቲከኞች ራሳቸውን ለሕዝብ የሚያስተዋውቁበት እና ያቀዱትን የፖለቲካ ፕሮግራም ለመራጩ ህዝብ የሚያስረዱበት እድል በመሆኑ በምርጫ ሂደት ዋነኛ ክፍል ነው፡፡

የምርጫ ቅሰቃሳ ዘመቻዎች የዲሞክራሲ ሥርዓትን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ መራጩን ህዝብ የማሳመኛ ሃሳቦች በልዩ ልዩ የሚዲያ መሳሪያዎቹ ማለትም በግል፣ በቴሌቭዥን እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ-ኢንተርኔት በሚለቀቁ ቪዲዮዎች ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች፣ አቤቱታዎች እና መግለጫዎችን አጠቃልሎ ይይዛል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ፕሮግራሞች እጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫው ቀን በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ሃገራዊ እና ርዕዮታዊ ዓለማዊ ጉዳዩች ላይ ሃሳባቸውን እና አቋማቸውን ለመራጮች የሚያቀርቡባቸው መድረኮች ናቸው፡፡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመራጮች ‹የምረጡኝ› መልዕክቶቻቸውን ለማድረስ የተለያዩ ቴክኒኮችን ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በተለምዷዊ እና አዲስ ሚዲያዎች፣ በህዝባዊ ዝግጅቶች፣ በሥነ ጽሁፍ፣ ቁሳቁሶች ወይም ሌሎች መንገዶች ይከወናሉ፡፡ ይፋዊ የምርጫ ቅስቀሳ አብዛኛውን ጊዜ ለአንድ ወር ወይም ብዙ ወራት የሚፈጀው ጊዜ እስከ ምርጫ ቀን ከመድረሱ በፊት ያለውን አካትቶ ይይዛል፡፡

*የቡድን መወያያ ጥያቄዎች*

***ወድ ሰልጣኞች!***

1. *የምርጫ ቅስቀሳዎችን ዘመቻ ማካሄድ ያስፈለገበትን ምክኒያቶች በዝርዝር ተወያዩባቸው?*
2. *በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ዋና ዋና ተዋናዮች እነማን ናቸው? ተግባራቸውስ?*
3. *የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ምን ምን ጉዳዮችን አካቶ ሊይዝ ይችላል?*

ዲሞክራሲያዊ ምርጫዎች በመረጃ የተደገፉ፣ እንዲሁም ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆኑ፣ እና ዕጩ ተወዳዳሪ ደጋፊዎቻቸው ነፃነት እንዲያገኙ እና የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን በነፃነት እንዲያስተዋውቁ ሰፊ ሠላማዊ የሆነ የፖለቲካ ሥነ-ምህዳር ያሥፈልጋል፡፡ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን መራጩ እንዲረዳቸው ፍትሃዊ የፖለቲካ ምህዳር ጭምር ያሥፈልጋል፡፡ እነዚህን ግቦች ለማሳካት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች ወሳኝ ናቸው፡፡ እውነተኛ ፉክክር ያለው ምርጫ ተወዳዳሪዎች ፖለቲካዊ አቋማቸውን ለዜጎች ለማስተላለፍ እና የህዝብን የይሁንታ ድምጽ ለማግኘት ፍትሃዊ እድል መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳዎች እጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች መልዕክታቸውን ለዜጎች እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ መራጮች በምርጫ ቀን በዕውቀት እና በመረጃ ላይ የተመሰረተ የምርጫ ውሳኔ እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡ እኩል የመጫወቻ ሜዳ በመፍቀድ የዜጎችን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ምርጫ እንዲካሄድ ለማገዝ ለምርጫ ተወዳዳሪዎች የሚመደብ ማንኛውም የህዝብ ሀብት ፍትሃዊ መሆን አለበት፡፡ ስለ የምርጫ ቅስቀሳዎች መረጃ ማግኘት፤ የህዝብ ሀብት ክፍፍልን ጨምሮ፤ ፓርቲዎች እና እጩዎች የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴዎቻቸውን ዕቅድ በመንደፍ፣ ከሃገራቸው ሃብት ምንያህል ለዚህ ሥራ ማግኘት እንደሚችሉ በመረዳት ግልፅ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መከተልን ያካትታል፡፡

ስለ ምርጫ ዘመቻዎች መረጃ ማግኘት ተወዳዳሪዎች እና ሲቪል ማህበረሰብ እጩዎች በማንኛውም አውድ ውስጥ የሚቀርቡትን ማንኛውንም የህዝብ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ግብአቶች በአግባቡ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለሚዲያ እና እንደ ሰልፍ ላሉ የዘመቻ ዝግጅቶች ቦታን ጨምሮ ፍትሃዊ ተደራሽነት ይኖራቸው እንደሆነ እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል (Farrell,1996.)፡፡

የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን ለተወዳዳሪዎች የተመደቡ ከሆነ፣ ፓርቲዎች፣ እጩዎች እና ዜጎች የምደባው ሂደት ተአማኒ እና በመንግስት የተሠጠው የአየር ሠዓት፣ የጋዜጣ አምድ ድልድል ፍትሃዊ መሆኑን መመርመር ይችላሉ፡፡ ለዘመቻ የሚሆን የህዝብ ሃብት ክፍፍል በሌለበት ሁኔታም ቢሆን ተወዳዳሪዎች እና ሲቪል ማህበረሰቡ ተፎካካሪዎች እንዴት ስራቸውን እንዲያከናውኑ እንደተፈቀደላቸው ኢ-ፍትሃዊ ወይም የተዛባ አያያዝ መኖሩን መመርመር ይችላሉ፡፡ ይህ ምናልባት የፓርቲ ቢሮዎች እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸው ወይም ለሰልፎች ወይም ለሌላ የቅስቀሳ ዝግጅቶች ፈቃድ በሌለው መንገድ መሰራጨቱን ወይም አለመሠራጨቱን ሊያካትት ይችላል፡፡ እነዚህ ሁነቶች  ግልጽነት ያለው አሰራር በተወዳዳሪዎች እና በመራጮች በኩል በምርጫው ሂደት ላይ መተማመንን ያሳድጋል፡፡

# ማጠቃለያ

የፖለቲካ ተግባቦት ማለት በመሪዎች፣ በመገናኛ ብዙሃን ወይም በዜጎች የተፈጠሩ ቋንቋ እና ምልክቶች በግለሰቦች የፖለቲካ ግንዛቤ፣ አመለካከት ወይም ባህሪ ላይ የታሰበ ወይም ያልታሰቡ ተፅእኖዎችን የሚፈጥሩበት ሂደት ወይም የአንድ ሀገር ህዝባዊ ፖሊሲን የሚመለከቱ ውጤቶችን የሚያሳዩበት ፖለቲካዊ ሥርዓተ መልዕክት ነው።

የ21ኛው ክፍለ ዘመን የፖለቲካ ተግባቦት በርካታ ውስብስብ የሆኑ ተያያዥነት ያላቸው ባህሪያት አሉት። በመጀመሪያ፣ በሶስት የፖለቲካ ተግባቦት ቁልፍ ተዋናዮች መካከል የስትራቴጂክ ወይም ተምሳሌታዊ ተፅእኖን ያካትታል። ይህም የፖለቲካ መሪዎች፣ ሚዲያ እና ሰፊውን ህዝብ አካትቶ ይይዛል። ሁለተኛ ደግሞ ፖለቲካዊ ተግባቦት የሚተገበረው በመደበኛ ሚዲያ መድረክ ነው። ሦስተኛ ፖለቲካ ቅስቀሳና ዘመቻዎች በሚተላለፉበት ሂደት ውስጥ ዲጂታል-ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። በአሁኑ ሰዓት ‹አምስተኛ መንግስት› እየተባለ የሚጠራው ሚዲያ፣ ልክ እንደ ሁሉም የመገናኛ ዘዴዎች፣ የፖለቲካ ተግባቦት ዓላማዎች፣ በአዎንታዊ እና አሉታዊ ውጤቶች ሊያመጣ ይችላል። ይህ ውጤት ሊያመጣ የሚችለው ግን በህግ እና ሥርዓት የመምራት ወይም ያለመምራት ጉዳይ ነው። ሚዲያ በህግ እና ሥርዓት ሲመራ ለአንድ ሃገር የዲሞክራሲ ሠራዓት ግንባታ ትልቅ የሆነ ጠቀሜታ አለው።

# ክፍል ሁለት

## 2. መራጮችን የማሳመን ፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ

### መግቢ፡-

በዚህ ክፍለ ትምህርት የፖለቲካ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻን አስመልክቶ መራጮችን የማሳመን አካሄድ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ ክፍለ ትምህርቱ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻን የማሳመን የተግባቦት ባህሪያት፣ መልዕክቱ እና የመልዕክት ተቀባይ የአመለካከት ለውጥ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩባቸውን መንገዶች እንድንመረምር ያግዘናል፡፡

የክፍለ ትምህርቱ መጀመሪያ ክፍል የሚያተኩረው በፖለቲካ መልዕክት አስተላላፊው ዋና ዋና ባህሪያት እና በፖለቲካዊ መልዕክቱ ላይ ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል የሚያተኩረው መልዕክት ተቀባይ የሆኑ መራጮችን፣ በማሳመን ፖለቲከኞች ሊኖራቸው የሚገባውን ዋና ዋና ባህሪያት እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛው ንዑስ ክፍል በፖለቲካ እሳቤያቸው ጠንካራ እና ጥልቅ ስሜት ያላቸው እና የሌላቸው መራጮች ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር ተግባራዊ የሚደረጉ መንገዶች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ መልዕክቶች በመራጮች አዕምሮ ውስጥ የበለጠ መደመጥ የሚችሉበት ስልቶች ለማሳወቅ እና ዕጩዎች በጣም አስፈላጊ በሆነ የድምፀ ውሳኔ ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ለማድረግ፣ መንገዶችን እንዲያደንቁ ለማገዝ የተቀረፀ ሲሆን ክፍለ ትምህርቱ ከቀደመው ምዕራፍ የበለጠ ሥነ-ልቦናዊ ግፊትን ይወስዳል፡፡ የፖለቲካ እጩዎች ስለምርጫ ቅስቀሳ መልዕክቶች በመራጩ ህዝብ ሥነ-ልቦና እንዴት ተቀባይነት ሊኖራቸው እንደሚገባ በውል ሳይገነዘቡ፤ መልዕክታቸውን በውል ሳይገመግሙ ብሎም ሳያውቁ በመራጮች ላይ የሚፈለገውን አወንታዊ ተጽዕኖ ማሳደር አይችሉም፡፡

**የክፍለ ትምህረቱ ዋና ዋና ዓላማዎች**

**ሰልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ ቡኋላ፡-**

- የማሳመን ትርጉምን ይረዳሉ፤
- ዋና ዋና የምርጫ ዘመቻ የማሳመን ብልሃቶችን ይገነዘባሉ፤
- የፖለቲካ ፓርቲዎች ‹የምረጡኝ› ዘመቻ የማሳመን ፋይዳውን ይረዳሉ፤
- አሳማኝ የፖለቲካ ተግባቦት ሂደቶችን ያውቃሉ፤
- የፖለቲካዊ ተግባቦት የማሳመን አተገባበር ይረዳሉ፤
- ዋና ዋና የሚባሉትን የምርጫ ቅስቀሳ ማሳመኛ መንገዶችን ይገነዘባሉ፣

## 2.1. ማሳመን (Persuasion) ምንድነው?

**ውድ ሰልጣኞች!**

1. *እናንተ በዕለት ከዕለት ህይወታችሁ ውስጥ ሰዎችን ለማሳመን ምን ምን ዘዴዎች ትጠቀማላችሁ?*
2. *በፖለቲካው ዓለም ውስጥ በማሳመን እና በፕሮፖጋንዳ መካከል ምን አይነት ልዩነት ያለ ይመስላቹሃል?*

ማሳመን አንዱ የፖለቲካ ተግባቦት ማዕከል ሲሆን መልዕክት አስተላላፊ ፖለቲከኞች፣ መልዕክታቸውን በንግግር፣ በፁህፍ፣ በምልክት.....ወዘተ በማስተላለፍ የራሳቸውን የፖለቲካ ፕሮግራም በሌሎች ዘንድ ትኩረት እንዲያገኝ ወይም ሌሎች የነበራቸውን ዕምነትና አስተሳሰብ

እንዲቀይሩ/እንዲያስተካክሉ ለማነሳሳት የሚሞክሩበት ተምሳሌታዊ ሂደት ነው። ማሳመን በተፈጥሮው ዕውነታን እና ምክንያታዊ መሆንን ይጠይቃል።

ማሳመን የሰዎችን የጋራ ፍላጎቶች ለማሟላት አመለካከቶችን፣ ሃሳቦችን፣ አቋሞችን፣ እምነቶችን እና ባህርያትን ለመለወጥ የሚደረግ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎችን አካትቶ ይይዛል። በስዎች መካከል የሚደረግ መተማመን በቀጥታ ማሳመንን ይነካል። በማሳመን ውስጥ ደግሞ ቃል መግባትንና የጋራ ውል ስምምነትን መውሰድ ይኖራል። ለማሳመን ተብሎ የማይተገበር ውልና ቃል ኪዳን መግባት ግን ለተናጋሪው የሥነ ምግባር ዝቅጠትን ያመጣል (Marshall, 2015)።

በፖለቲካው ዓለም ውስጥ አሳማኝ መልዕክት ተናጋሪውን ብቻ ሆን ተብሎ ለመጥቀም ሲነደፍ ወደ ፕሮፓጋንዳ ወይም ማስገደድ ይሸጋገራል። ፕሮፓጋንዳ፣ የፕሮፓጋንዳውን ተናጋሪ መልዕክት ለሚያሰራጩ ተቋማት (በተለምዶ የመንግሥት ወይም የድርጅት) ዓላማዎች መሠረት በማድረግ የሕዝብን አስተያየት ለማወናበድ ስልታዊ እና ሆን ተብሎ የሚደረጉ ሙከራዎችን ያካትታል።

ማሳመን ስኬታማ ለመሆን 'ተናጋሪው' በሚናገረው ጉዳይ/ሁናቴ ላይ ፅኑ ዕምነት ወይም አመለካከት ማዳበር ያስፈልገዋል። ይህንን ማድረግ ሲችሉ ተናጋሪዎች ንግግራቸው ለታለመው ታዳሚዎች ትኩረት፣ ተነሳሽነት እና ጨዋነት (ታዋቂነት) ያመጣል። የአሳማኝ ተናጋሪዎች ክርክራቸውን ለማጠናከር የማህበረሰቡን ሥነ-ልቦና እሴቶችን እና አመለካከቶችን በመቀበል መተማመን እና መቀራረብ ይገነባሉ። በሚናገረው ጉዳይ ላይ ፅኑ ዕምነትና ውስጣዊ አቋም ያለው ተናጋሪ አስቀድሞ ወደ ሰዎች ሥነ ልቦና ውስጥ የገባ በመሆኑ፣ አሳማኝ መልዕክቱ በተፈጥሮ ከራስ የመነጨ እንደሆነ ይገነዘባል። ብዙውን ጊዜ እንደ አንድ የጋራ አስተሳሰብ ይመሰላል።

Schwartz (1974) የተባለው ፀሃፊ ማሳመንን መልዕክቱ ታዳሚው ምን እንደሚያስብ፤ ምን ሊሠማው እንደሚችል ቀድሞ በመረዳት የሰዎችን ስሜት በመቀስቀስ፣ ወደ ተናጋሪው ዓላማና ፍላጎት ሠዎችን የመሳብ ጥበብ ነው በማለት ይገልፃል።

***ለመሆኑ በማሳመን እና በፕሮፖጋንዳ መካከል ምን አይነት ልዩነት አለ?***

ፕሮፓጋንዳ 'መላውን ሰዎች ለመያዝ' ይሞክራል፡፡ በተፈጠረው አፈ-ታሪክ፣ ፕሮፓጋንዳ ሙሉ በሙሉ ሊታወቅ የሚችል እውቀት ብቻ ያስገድዳል፣ ይወስናል፡፡ በባህሪው ለአንድ ትርጓሜ ብቻ የሚጋለጥ ነው፡፡ ነገር ግን ማሳመን ለሀገራዊ እሴቶች፣ ማህበራዊ ህልሞች ወይም የህብረተሠቡን ሃይማኖታዊ ምክንያቶች ማወቅና መካንን ይጠይቃል፡፡ 'የተደራጀ ተረትና ምሳሌ' እንደ ተናጋሪው እምነት ይሠራል፡፡ ማለትም የህብረተሰቡ ዕሴቶች አሳማኝ ክርክርን ለመግለጽ እና ለመገደብ እንደ ዋና ምክንያት ሆነው ያገለግላሉ ለማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ማሳመን ወደ ፕሮፓጋንዳ የሚቀየረው እያወቀ ሲያሳስት ወይም እምነቶችን፣ እሴቶችን እና አመለካከቶችን ለፕሮፓጋንዳው ጥቅም ሲያውሉ ነው፡፡

## 2.2. ዕጩዎች መራጮችን የማሳመን ሂደቶች

በፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች መካከል በፖሊሲ አማራጮች፤ የፖለቲካ ፕሮግራም እና በርዕዮተ-ዓለም፤ የሚደረግ የምርጫ ቅሰቀሳ እና ክርክር በምርጫ ወቅት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይህ በፓርቲዎች መካከል የሚደረግ ፖለቲካዊ ክርክር መራጩ ህዝብ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አቋም፤ ፕሮግራም፤ ርዕዮተ ዓለም፤ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በውል እንዲረዳ ያደርጋል፡፡

ዕጩዎች መራጮችን የማሳመን ሂደቶች የተለያዩ ብስለት ያላቸው ሃሳቦችን፣ መራጩ ህዝብ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች/ውኪሎች በማንሳት ብቃት ያላቸውን ዕጩዎች በውል እንዲገነዘብ ሰፊ እድል ይሠጣል፡፡ ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ክርክር መድረክ ላይ የፓርቲኣቸውን አቋም በደንብ በተደራጀ፤ በአንደበተ ርዕቱነት፣ ብስለት እና ብልጠት በተሞላበት መልኩ የመራጩን ቀልብ መሳብ በሚያስችል የጠራ፤ ግልፅ የሆነ ሃሳብ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም መራጩ ህዝብ በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በንቃት የሚከታተለው የትኛው ፓርቲ ምን ዓይነት የፖለቲካ ዓላማና ፕሮግራም አለው/አላት…? ማን ዕጩ ምን አለ/ች…? የመሳሰሉትን ጥቄዎች በማንሳት መደበኛ ባልሆነ መልኩ ውይይት ያደርጋል፡፡

በሃገራዊ የምርጫ ክርክሮች ውስጥ ሁለት ጎን መልዕክት ለተቃዋሚው በትክክል መቃወሙን/ሚን መልስ የሚሰጥ ነገር ግን በምክንያት እና ማስረጃ የሚቃወም፣ በመራጩ

ህዝብ በአመለካከት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መልዕክት መቅረፃችን በትክክል የሚያሳይ ምላሽ መስጠቱን ማሳየት አለበት፡፡

ሥለዚህ ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ ክርክር መድረክ ላይ ለመራጩ ህዝብ የምናስተላፈው መልዕክት፣ ዋናው ሃሳብ በራሱ የመራጩን ህዝብ ትኩረት የሚማርክ፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የመራጬን ህይወት የሚነካ ጉዳዮች የሚዳስስ፣ አንደበተ ርዕቱ መሆን፤ ተገቢ ስብዕና እና አለባበስ፤ በልዩ ልዩ ሚዲያዎች የፓርቲው የዜና ሽፋን እንዲኖረው ማድረግ፤ የመራጬን ህዝብ ቀልብ የሚስብ የንግግር ችሎታን (oratorical skills) ማዳበርን እና መላበስን ወዘተ.......የመሳሰሉትን ይጠይቃል፡፡

በዓለማችን ሥለ ውጤታማ ፖለቲካዊ ተግባቦት የክርክር ዘመቻ፣ የማሳመን ስልት አንድ ዓይነት ወጥ የሆነ ፍጹም ትክክለኛ አካሄድ ቀመር የለም፡፡ የምርጫ ክርክር ዘመቻዎች ፖለቲካዊ ተግባቦት ስልት እንደ ቼዝ ጨዋታ ከሁኔታዎች ጋር ተለዋዋጭ ናቸው፡፡ አቋሞች እና ሃሳቦች ሁል ጊዜ ይለዋወጣሉ፡፡ አጠቃላይ ግን ብዙዎች የሚስማሙባቸው የፖለቲካ ተግባቦት ክርክር ዘመቻ መራጮችን የመሳመን ስልቶችን ቀጥለን እንመልከት፡-

- የመከራከሪያ ዋና ሃሳብ እና ንግግራችንን አጭር፤ግልፅ እና ቀላል ማድረግ፤
- አዕምሯዊ ምስል ከሳች አባባሎች እና አገላለፆችን መጠቀም፤
- ልዩ ልዩ ሀገራዊና ወቅታዊ ክስተቶችን በውል መረዳትና ለነሱ ምላሽ የሚሠጥ ፖለቲካዊ መፍትሄ ማስቀመጥ፤
- ስለ እውነተኛ ሰዎች የስኬት ታሪኮችን መናገር፤
- በሌሎች ምላሽ ቁጡና በቶሎ የሚበሳጩ አለመሆን፤ ይልቁን ለተነሱ ሃሳቦች በተረጋጋ መንፈስ ተገቢና ምክኒያታዊ ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀት፣
- ንቁ መሆን እና ተሳታፊዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች በሚገባ ተረደቶ ተገቢውን ማብራሪያ መስጠት፣
- ንግግራችን በትክክለኛው የሃሳብ ፍሰትና ቅደም ተከተል ማቅረብ፤አለመዘበራረቅ፣

በአጠቃላይ የፖለቲካዊ መራጮችን የማሳመን ዘመቻ ስልት እና እቅድ ማውጣት፣ ምን እንደምንናገር፤ ለማን እንደምንናገር፤ መቼ እንደምንናገር፤ ምን አይነት የፖለቲካ ፕሮግራም እና አሰላለፍ ካላቸው ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እንደምንከራከር/እንደምንወያይ፣

ማወቅ እና ቅድመ ዝግጅትን ማድረግ ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ተወዳዳሪያችን/ተፎካካሪያችንን ለማሸነፍ የተፎካካሪያችንን ፖለቲካዊ ሃይል አሠላለፍና አካሄድ በውል መረዳት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

## 2.3. የማሳመን ብልሃቶች

ከላይ እንደተመለከትነው የውጤታማ የፖለቲካዊ ማሳመን ጥበብ የማዕዘን ድንጋይ ተአማኝነት ነው፡፡ ተአማኝነት ያለው ምስል ከሳች መልዕክት ማስተላለፍ እና በፖለቲካዊ አመራር ላይ ጥሩ ግንዛቤን ማዳበር ጠቃሚታው ከፍተኛ ነው፡፡

ሦስቱ ቁልፍ የማሳመን ብቃታችንን ከፍ የሚያደርጉ ዋና ዋና ፍሬ ጉዳዮች ደግሞ ሙያዊ እውቀት፣ ታማኝነት እና በጎ ፈቃደኝነት ናቸው (McCroskey & Teven 1999)፡፡

እውቀት ስንል ተናጋሪው ለፖለቲካ የተካነው ወይም የተላበሠው ብሎም የተሰጠው እውቀት ነው፡፡ ይህም የፖለቲካ ልምድ እና ችሎታን አካቶ ይይዛል፡፡ ፖለቲከኛው በመስኩ ተገቢውን ልምድ እና እውቀት በማካበት የመራጩን ህዝብ ዓይንና ትኩረት መሳብንም ጭምር አካትቶ ይይዛል፡፡

የተአማኝነት ጠቀሜታን አርስቶትል እንደሚከተለው አብራርቶታል፡፡ እሱም "ethos" የሚለውን ቃል ታማኝ ተግባቢዎችን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፡፡ ለበርካታ አስርት አመታት የተካሄዱ የተጨባጭ ጥናቶች አንድ አይነት ታማኝነት (Credibility) አለመኖሩን ወይም ተአማኚነትን ለመራጩ ህዝብ ለመግለፅ አንድ መንገድ አለመኖሩን በርካታ የጥናት ውጤቶች አረጋግጠዋል፡፡

ታማኝነት ማለት ፖለቲካ ተናጋሪው ለሚነገረው ሃሳብ ያለውን ታማኝነት እና ቅንነት፤ መልካም ሥነ-ልቦና፤ ባህሪ፤ ደህንነት እና የሚናገረው ሰው ምን ማለቱ እንደሆነ እና ምን ለማጋራት፤ መልዕክት ለማስተላፍ ለመናገር ቅድመ-ዝንባሌውን፤ በጎ ፈቃድን፣ ለመራጩ ህዝብ ያለውን እንክብካቤ፣ መተሳሰብን እና የሌሎችን ችግር መረዳትን ያመላክታል፡፡ ታማኝነት የፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ማሳመን ቁልፍ አካል ነው፡፡ በተጨማሪም የተዓማኚነት ባህሪያት በተለያዩ የምርጫ አውዶች ውስጥ የመጠቀም ልምድን ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሴቶች ከወንዶች የበለጠ በመራጩ ህዝብ ዘንድ ታማኝ እንደሆኑና፣ በታማኝነታቸው የማሳመን ብቃታቸው ከወንዶች የተሻለ እንደሆነ የብዙ የጥናት ውጤቶች ያረጋግጣሉ፡፡

የዘርፉ ባለሞያዎች እንደሚመክሩት ማሳመን ብልሃቱ እና ስልቱ የተለያየ ነው። አንድ ዓይነት የማሳመን ባህሪ በሁሉም የምርጫ ቅሰቀሳዎች እንደማይሰራ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በምትኩ እንደ የምርጫው ባህሪ፤ እንደምናሳምነው የማህበረሰብ ክፍል ንቃተ ህሊና፣ እንደ አካባቢው ሁኔታ እና ባህል የሚወሰን ሆኖ፣ የተለያዩ የታአማኒነት ገጽታዎች በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት መላበስ ተገቢ ነው።

ልክ እንደ ታማኝነት በጎ ፈቃደኝነትን፣ ለመራጩ ህዝብ አክብሮት ማሳየት ተገቢ ነው። ነገር ግን ስሙ እንደሚያመለክተው በጎፈቃድ፣ ርህራሄ እና እጩ ተወዳዳሪው ለመራጮች እንደሚያስብ እምነት ሊጣልበት እንደሚችል ያተኩራል። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ኦባማ እንደዚህ አይነት የግል ሰው በመሆናቸው ለመራጮች እንደሚያስቡና ርህራሄ እንደላቸው መልዕከት ማስተላለፍ ችለዋል። በሚያስደንቅ ሁኔታ ይህንን በጎ ፈቃደኝነታቸውን ለህዝባቸው በማሳየታቸው ማሸነፍ ችለዋል። ምክንያቱም ዕጩ ሆነው ለደሃው የማህበረሰብ ክፍል የጤና አጠባበቅ እቅድ "ኦባማኬር" በሚሊዮን የሚቆጠሩ አሜሪካውያን ጤና ዋስትና ብለው የሚጠሩት በማስተዋወቃቸው እና በጎ ፈቃደኚነታቸውን ለመራጮች በማሳየታቸው ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት መሸነፍ ችለዋል።

## 2.4. የፖለቲካ ትረካዊ የምርጫ ቅስቀሳ የማሳመን ስልት

ትረካዎች በማህበራዊ አመለካከቶች ላይ ጠንካራ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ዕጩዎች የወደፊት የሃገራቸውን ብሩህ እይታዎችን በትረካዊ የምርጫ ቅስቀሳ ስልት ሊያቀርቡ ይችላሉ። ምክንያቱም ትረካዎች በመራጮች ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው (Bilandzic & Busselle፣ 2013)።

እጩዎች በአስደናቂ ትረካዎች ዙሪያ ጉዳዮችን በመቅረጽ ምርጫን ያሸንፋሉ። በምርጫ ያሸነፈው እጩ ምርጥ ትረካዊ ስልት ተጠቅሟል ማለት ግን ድምፅ ለማግኘት ተረት ፈጥሯል ማለት አይደለም። ዋናው ነጥብ የፖለቲካ ትረካዎች መራጮች በእለት ከዕለት የገጠማቸውን ፖለቲካዊ ችግሮችን የሚገልጹ ድራማዊ ዘዴዎችን መያዙ ነው። ፖለቲካዊ ችግሮችን መፍትሄዎችን መስጠት በተወሰነ ደረጃ ምርጫዎች ለመራጮች የእኛን ፖለቲካ ዓላማ በአንድ መነጽር እንዲመለከቱ ማሳመን ነው። ለምሳሌ፡ በእኛ ሃገር በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ

ገድሎችን የፈፀሙ ጀግኖች አሉ። ታዲያ የእነዚህን ጀግኖች ለችግር አይበገሪነታቸውን ከአካባቢው ማህበረሰብ ሥነ ልቦና ጋር በማዋሃድ የእኛን የፖለቲካ አላማ ጠቅሶ መቅረብ።

የምናቀርባቸው መልዕክቶችም በሌሎች ዘንድ አሳማኝ እንዲሆኑ ካስፈለገ ምክንያታዊ፣ ዕውነታዊ እና ተጨባጭ ፖለቲካዊ ትረካዎች ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። በጣም የተለየ ምክንያታዊ ታሪካዊ ማስረጃ የእጩዎችን ተአማኒነት ሊያሳድግ እና ለመልዕክታቸው ግንዛቤን መስጠት ይችላል። እጩዎች የቁጥር እውነታዎችን ወይም እነዚያን እውነታዎች በመደበኛነት ያብራራሉ።

## 2.5. የፖለቲካዊ ተግባቦት የማሳመን አተገባበር

**ውድ ሰልጣኞች!**

1. *ፖለቲካዊ ማሳመን ብቃታችንን ተጠቅመን እንዴት በመራጮች ትኩረት ውስጥ የራሳችንን ፖለቲካዊ ዓላማ ማሳካት እንችላለን?*
2. *ዕጩዎች/ፖለቲከኞች የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ መልዕክቶችን እንዴት ማስተላለፍ አለባቸው?*
3. *መራጮች በእጩ ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲቀይሩ ወይም እንዲያጠናክሩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?*

የማሳመን የመጨረሻ ነጥብ የመራጩ ትኩረት እና ቀልብ ወደራሳችን ወደ ምንፈልገው የእኛ የፖለቲካ ፕሮግራም ማምጣት ነው። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ መራጮች የሚያስቡትን፣ የያዙትን ስሜት እና በምርጫ ቀን ለማን እንደሚመርጡ ማሰብ ተገቢ ነው። የመራጮች የፖለቲካ ቅስቀሳ የዘመቻ መልዕክቶችን እንዴት መነገር አለባቸው? በእጩ ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲቀይሩ ወይም እንዲያጠናክሩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ቀድሞ ማሰብ ለነዚህ ጥቄዎች መልስ ለመሥጠት ቀድሞ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።




*ምስል.3. የፖለቲካዊ ተግባቦት የማሳመን አተገበባር*

አሳማኝ የመከራከሪያ ነጥቦችን ለመቅረጽ፣ አሳማኝ ሰዎች ስለ አሳማኝ መልዕክቶች እንዴት እንደሚናገሩ እና እንዴት እንደሚያስረዱ መረዳት አለባቸው፡፡ ዋናው ነገር የፖለቲካ ተሳትፎ ወይም ዘመቻ የሚታወቅበት ወቅት፤ በግል ደረጃ ለመራጩ ህዝብ ተዛማጅ እና ቅርብ መሆን ወይም የገጠማቸውን የዕለት ከዕለት ልዩ ልዩ ጉዳዩች በግል በማንሳት የሚያስከትሉትን ውጤቶች መንካት እና እያነሱ ከነሱ ጋር መወያየት አስፈላጊ ነው፡፡

በዕለት ከዕለት በመራጩ ህዝብ ህይወት ውስጥ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳለ በመገንዘብ፤ ፖለቲካዊ መልዕክቶችን በተለያየ መንገድ እና ስልት ማስኬድ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ በሃገራችን በአርሶ አደሩ አካባቢ እና ተማሪ በምንለው የህብረተሰብ ክፍል ፖለቲካን የሚረዳበት እይታ እና ተሳትፎ የተለያየ ስለሆነ የምናነሳቸው ጭብጦችና መልዕክቶች ቀድሞ ማሰብ፣ ማቀድ እና መዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ መራጮች ከሚያስቡት ጋር ለመመሳሰል የፖለቲካ አሳቢዎች ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ተሳትፎ ላላቸው ግለሰቦች የተለያዩ መልዕክቶችን ዕጩዎች መንደፍ አለባቸው፡፡

ቀጥለን ሁለት አይነት ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች እንዴት ፖለቲካዊ ማሳመንን አካሄድ ልንተገብር እንደምንችል እንመለከታለን፡፡

### 2.5.1. ዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸው መራጮች የማሳመን አተገባበር

ውድ ሠልጣኞች!

*1. እጅግ በጣም አነስተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ባላቸው የህ/ሰብ ክፍል የምርጫ ቅስቀሳን ማሳመንን እንዴት ልታከናውኑ ትችላላችሁ?*

*2. እጅግ በጣም ከፍተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ባላቸው የህ/ሰብ ክፍል የምርጫ ቅስቀሳን እንዴት ልታከናውኑ ትችላላችሁ?*

አልፎ አልፎ አንዳንድ ጊዜ የመምረጥ ዕድል ያላቸው መራጮች በዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ እና መነሳሳት ላይ ሆነው የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻውን በንቃት መከታተል ላይ እምብዛም ፍላጎታቸውን አያሳዩም፡፡ በእነርሱ ዕይታ ምርጫው የራሳቸውን የግል ሕይወት እንደማይመለከት በማመን ወይም የነሱን መሠረታዊ ዕሴቶችን እንደማይነካ በመመልከት፣ የመራጮች ቅስቀሳ ዘመቻ ለመከታተል መነሳሳት ይጎድላቸዋል፡፡ ድምጽ ለመስጠት ካቀዱም በአጭሩ እና ቀላል ስልቶች ይተልማሉ፡፡ ሃገራዊም ሆነ አካባቢያዊ ምርጫዎች ለእነሱ ትልቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ የእጩዎችን መልዕክት በማሰላሰል ብዙ የአዕምሯዊ ጥረት አያደርጉም፡፡

ታዲያ ለነዚህ ዓይነት መራጮች፣ ዕጩዎች/የእጩ ወኪሎች ዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸውን መራጮች ለማሳመን ብዙ የአዕምሮ ሂደት የማይጠይቁ ቀላልና አጭር መልዕክቶችን መንደፍ አለባቸው፡፡ የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች እነሱ ያለፉትን ልምድ እና ተሞክሮ የሚነኩ ቀላል ምልክቶች ከመራጮች ምርጫ ጋር ማዛመድ ተገቢ ነው፡፡

የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ውይይት እና ክርክሮች ለመከታተል  ብዙም ፍላጎት የሌላቸው መራጮች ‹‹ያገባናል››፣ ‹‹እመርጠዋለሁ›› የሚሉት እጩ ከሆኑ፣ በቁም ነገር ውስጥ መሳተፍ አይፈልጉም፡፡ መልዕክታችንን በፅሞ እና ትኩረት ሠጥተው አያስተናግዱም፣ አያዳምጡም፡፡ ለመስማት ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ ይልቁንስ  አጭር የሆነ መልዕክታችንን በፍጥነት እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ከመራጮች ዝቅተኛ  የፖለቲካ ስሌት ጋር የሚያገናኙ ቀላል መልዕክቶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በዝቅተኛ  ፖለቲካዊ ተሳትፎ ላሉ የህ/ሰብ ክፍሎች የምናደርገው የማሳመን አካሄድ እጩዎች የሚሳካላቸው እንደዚህ ያሉ ቀላልና አጭር መልዕክቶችን ሲያጎሉ ነው፡፡

ታዋቂ ፖለቲከኞች፣ ተዋቂ አትሌቶች፤ የንግድ መሪዎች ወይም ታዋቂ ሰዎች እጩውን ድጋፍ ሊሠጡ ይችላሉ፡፡ ዝቅተኛ ተሳትፎ ያላቸው መራጮች የተከበረ ታዋቂ ግለሰብ ዕጩውን/ዋ ስለደገፈው እነሱም ተዋቂውን ግለሰብ ተከትለው እይታቸውን ወደ እጩ ሊያዘነብሉለት ይችላሉ፡፡ በእጩ እና እንደ ባንዲራ፣ ቤተሰብ ባሉ ምልክቶች መካከል ያሉ አዎንታዊ ግንኙነቶች አንስቶ ማብራራት፤ የእጩው የንግግር ድምጽ ማራኪነት፤ አካላዊ ማራኪነት፤ የአለባበስ ወይም ከፕሮቶኮል፣ ፖለቲካዊ ግርማሞገስ፤ በመገናኛ ብዙሃን የሚያስተላልፈው መልዕክት ማራኪነት፤ አንዳንድ ዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸውን መራጮች ለማነሳሳት በቂ የማሳመን ስልት ሊሆኑ ይችላል፡፡ በእጩ እና በመራጮች መካከል በዘር፣ በጾታ ወይም በጎሳ መካከል ያለው ተመሳሳይነት ጭምር ያካትታል፡፡ በማይክሮ ኢላማ የተደረገ የፌስቡክ ፖስት ጓደኛሞች እጩውን "እንደሚወዱ" ከገለፁ እነሱም ሊያደንቁና ሊመርጡ ይችላሉ፡፡

***<u>የቡድን መወያያ ጥያቄዎች</u>***

***ወድ ሠልጣኞች!***

*መራጮች ዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ባለባቸው ምርጫዎች እንዴት ድምጽ እንደሚሰጡ በሚወስኑ እንደ ውጫዊ ገጽታ እና ዝና ባሉ ምልክቶች ላይ ሲመሰረቱ ዲሞክራሲ ይከበራልን? ለምን? እነዚህ ምክንያታዊ የውሳኔ አሰጣጥ ስልቶች አይደሉም ብለው ክስ ማቅረብ ይቻላልን? የፖለቲካ ሚዲያዎች ዝቅተኛ ተሳትፎ ያላቸውን መራጮች ያታልላሉ? ወይስ መራጮች የእጩዎችን ‹ድምፃቹህን ስጡን› ተረድተው ውሳኔያቸውን በፍጥነት እና በቀላሉ ለመወሰን ያግዛሉ?*

## 2.5.2. ከፍተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸውን መራጮችን የማሳመን አተገባበር

መራጮች በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከፍተኛ ተሳትፎ ሲኖራቸው፣ ስለ ፖለቲካዊ መልዕክቶች የሚያስቡት በተለየ መንገድ ነው፡፡ የምርጫውን ውጤት የዕለት ከዕለት ኑሯቸውን እንዴት ሊነካ እንደሚችል በጥንቃቄ ያስባሉ፡፡ የምርጫው ውጤት የሃገራቸውን የቀጣይ ዕጣ ፋንታ፤ የስራ፣ የማህበራዊ፤ የፖለቲካዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ደህንነት ሁኔታ ፖለቲካው እንዴት እንደሚነካ በእጅጉ ያሳስባቸዋል፡፡ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ መልዕክቶች ላይ ትልቅ ትኩረት ይሠጣሉ፡፡

የግል ጥቅም በስልጣን ላይ ያለውን ተፅዕኖ በውል ይገነዘባሉ፡፡ በተለይ የሃገር መሪ የሚገመግሙት በሚያቀርበው የሃሳብ-ልዕልና/ድርጊት ሲሆን ይህም በአመለካከታቸው ላይ የተወሰነ አሉታዊ/አዎንታዊ ስሜቶችን ለውጥ ያመጣባቸዋል፡፡ የእጩን ስም ብዙ ጊዜ በመደጋገም ለህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት፤ ለሚኒስትርነት፤ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እና ለሴኔት በብዙ እሽቅድምድም ውስጥ አዕምሯቸው ውስጥ በማሠላሠል ያሰባሉ፡፡

ማስታወቂያ በተለይ በፓርላማ ውድድር ላይ ዜና እና ፖለቲካዊ ክርክሮች ብዙም ተጽእኖ በውሳያቸው አይፈጥርባቸውም ምክንያቱም ቀድመው ያውቃሉ (West፣2014)፡፡ በመሆኑም መራጮች ጠንካራ የፖለቲካ ፍላጎት ተሳትፎ ሲኖራቸው ለዕጩዎች/ለፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች እነዚህን መራጮች ማሳመን ቀላል አይሆንም፡፡

ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች ሰዎች የራሳቸው የሆነ ጠንካራ የፖለቲካ አመለካከት ወይም የፓርቲ ትስስር ስላላቸው መልዕክቶች ጆሮ ሠጥተው ላያዳምጡን ይችላሉ፡፡ ጠንካራ አመለካከቶች ከምሳሌያዊ እና ከዋና ማህበራዊ እሴቶች ጋር ትስስር አላቸው፡፡ እንደነዚህ ዓነት መራጮች ለራሳቸው ሁልጊዜ ትክክል እንደሆነ እርግጠኞች ናቸው፡፡ እንደነዚህ አይነት መራጮችን ማሳመን ሁልጊዜ ላይሳካ ይችላል፡፡

በእርግጥ ጠንከር ያሉ አመለካከቶች በራሳቸው በረከትም፣ እርግማንም ናቸው፡፡ ጠንከር ያሉ አመለካከቶች ሰዎች በፖለቲካው ውስጥ እንዲሳተፉ እና ለለውጥ እንዲሰሩ ያበረታታሉ ነገር ግን ግለሰቦች በጉዳዩ ላይ አማራጭ አቋም እንዳይዙ ያደርጋቸዋል፡፡ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ጠንካራ አቋም ሲኖራቸው፣ ከነርሱ ጋር የተያያዙትን ነገሮች በሙሉ በአንድ አይነት አመለካከት

በራሳቸው መነጽር/ዕይታ ብቻ ያዩታል፡፡ ጠንካራ አመለካከትን የታጠቁ ሰዎች ነገሮችን በአንፃራዊነት /Relativism/ አይመለከቱም፡፡

በዚህም የተነሳ ጥልቅ ግላዊ እና ብዙ ጊዜ አማራጭ የአመለካከት ነጥቦችን ለማገናዘብ ፈቃደኛ ያለመሆን ባህሪይ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ ጠንካራ ወገንተኞች ምሁራዊ እምነታቸውን ወደ ጎን በመተው በሚወዷቸው ቡድናቸው የተደገፈ አቋም እስከመስጠት ድረስ ለፖለቲካ ፓርቲያቸው ጥብቅ ታማኝ የመሆን ባህሪይ ይስተዋልባቸዋል (Cohen, 2003)፡፡

*የቡድን መወያያ ጥያቄዎች*

1. *ስለዚህ ጠንካራ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች እንዴት ማሳመን ይቻላል?*
2. *ጠንካራ የሆነ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ዜጎች ቀድመው ስለ እጩዎቹ መረጃ ሳላቸው እንዲህ አይነት መራጮችን እንዴት ማሳመን ይቻላል?*
3. *እጩዎች መራጮችን ከጠንካራ ወገንተኝነት ጋር ለማንቀሳቀስ እንዴት ይሞክራሉ? መልሱን በቡድን ተወያዩበት*

የማሳመን ጽንሰ-ሀሳቦች በጠንካራ አቋም ላይ ያለው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ከሁሉ የተሻለው መንገድ ተለዋዋጭነቱን እና የተናጋሪውነ የሃሳብ አወቃቀር ማድነቅ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ያስምሩበታል፡፡ የማህበራዊ ዳኝነት ፅንሰ-ሀሳብ አፅንዖት የሚሰጠው፣ ሰዎች በክርክር ውጤታቸው ላይ በመመስረት ግንኙነትን በተጨባጭ እንደማይገመግሙ ነው፡፡ ይልቁንም የተሟገተውን አቋም ከራሳቸው አመለካከት ጋር በማነፃፀር የራሳቸውን ማህበራዊ ፍርዶች

በማመሳሠል ይሠጣሉ፡፡ ማህበረሰቡ ባጠቃላይ ከሚያምኑት ጋር የሚመሳሰል ከሆነ መልዕክቱን ይቀበላሉ፡፡ በተጨማሪም በጉዳዩ ላይ ጠንካራ የአሸናፊነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን ተናጋሪው ከአስተያየታቸው የተለየ ማለትም የሚመስለውን አቋም ከወሰደ፣ የተናጋሪውን አቋም ከራሳቸው ያርቃሉ ወይም ይቃረናሉ፡፡ በመቀጠልም የሚያግባባውን ሃሳብ በጥቅሉ ውድቅ ያደርጋሉ፡፡

ስለ አንድ ጉዳይ ለምሳሌ፡- አከራካሪና አወዛጋቢ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዩች ማለትም ‹‹የብሄር ፖለቲካ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሃገራት ይጠቅማል ወይም ይጎዳል›› ያሉ ጉዳዩች የመራጮችን አመለካከት ለመቀየር አለመሞከር ተገቢ ነው፡፡ ይልቁንስ በርዕሱ ላይ አመለካከታቸውን እንዲያጋሩ ዕድል መስጠት እና ተናጋሪውን በፅሞና ማዳመጥ ነገር ግን መራጩን ለማሳመን አለመሞከር፡፡ መራጩ/ዋ የሰጡትን ሃሳብ በእጩው/ዋ ላይ እንደማይስማሙ የሚያመለክት አድርገው እንዳይተረጉሙ መጠንቀቅ፣ ስለምትናገሪው ነገር መጠንቀቅ ያሥፈልጋል፡፡ በእርግጠኝነት እጩዎች በጉዳዩ ላይ ግልጽ የሆነ ርዕዮተ ዓለም ወይም የፖለቲካ ፕሮግራም አቋሞችን ይኖራቸዋል፡፡

እንደ አጠቃላይ ግን በተለያየ ደረጃ የሚሰየሙ እጩዎች ለተወሰኑ መርሆዎች ይቆማሉ ግን እነሱ በጥንቃቄ መሆን አለባቸው ነው፡፡ ምክንያቱም መራጮችንና የደጋፊዎችን አዝማሚያ በውል መረዳት ስለሚያስፈልግ ነው፡፡ ምክኒያቱም ያለመራጮች ድጋፍ እና ድምፅ በምርጫ ማሸነፍ አይቻልምና፡፡  ለምሳሌ በእኛ ሃገር ደረጃ የብሄር ጉዳይ ትልቅ የፖለቲካ ትኩሳት ነው፡፡ ሥለዚህ ይህ ትኩስ ጉዳይ ምንም እንኳ የብሄር ፖለቲካን የምንደግፍ ወይም የምንቃወም ቢሆንም ጉዳዮችን ሲገልጹ በጥንቃቄ መሆን አለበት ነው፡፡ አለበለዚያ መራጮችን በማሰቀየማችን ድምፅ ያሳጣናል ነው በአጭሩ፡፡

*ለምሳሌ፡-ኦባማ እ.ኤ.አ. በ2008 መጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ አሜሪካዊ ፕሬዚዳንት ነው፡፡ በውስጡ ዘረኝነትን አምርሮ ይጠላል፡፡ የጥቁር አሜሪካውያን ጉዳይ እንደሚያሣስበው በገለፀ ማግሰት በመረጡት ነጭ መራጮች ላይ ትልቅ ቁጣን አትርፏል፡፡ ደግነቱ ይህንን ሀሳባቸውን የገለፁት ምርጫ ካሸነፈ በኋላ ነው፡፡*

በአጠቃላይ ሁሉም የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ መልዕክቶች መቶ በመቶ የመራጮችን አመለካከቶችን ለመለወጥ ወይም ለመቀየር አይደለም። አንዳንድ የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ መልዕክቶች አቋምና እምነትን ለማጠናከር ይሞክራሉ።

## 2.6. የምርጫ ቅስቀሳ የማሳመን ዘመቻ ዋና ዋና መንገዶች

**ወድ ሠልጣኞች!**

*በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ደጋፊዎችን/መራጮች ከእኛ የፖለቲካ ፕሮግራም ጎን፤ ምን ምን መንገዶችን ተጠቅመን ማሠለፍ እንችላለን?*

የምርጫ ቅስቀሳ ማሳመን በመረጃ የታገዘ ሲሆን ፖለቲካዊ ስኬትን ከፍ ያደርጋል። የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ መረጃ፣ ስለ ህዝባዊ የምርጫ ዘመቻዎች የጊዜ ሰሌዳ እንዲሁም የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ደንቦችን ወይም ገደቦችን ያካትታል። መረጃ በፓርቲ እና በእጩ ስራዎች ላይ እንደ ቦታ የመስራት ችሎታ ያሉ ለህዝብ ይፋ መደረግ ያለባቸውን መረጃዎችን ያካትታል። ተጨማሪ የዘመቻ መረጃ ተወዳዳሪዎች ለምርጫው ተመደበን የጋራ ሃብት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በግልፅ ያሳያል። ለምሳሌ ሚዲያ ወይም የህዝብ ቦታዎች አጠቃቀምን ያካትታል። ስለ ሚዲያ ድልድል መረጃ ከውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ጋር የተገናኘ መረጃን ያካትታል (ለምደባው ጥቅም ላይ የዋለው ስርዓት እንደ ሎተሪ) እና ውጤቶችን ነው። አግባብነት ያለው መረጃ የድጋፍ ፍቃዶችን በተመለከተ ስለ ማመልከቻዎች መረጃን ሊያካትት ይችላል። ማን እንዳመለከተ፣ መቼ፣ ለምን፣ ማመልከቻው ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም መከልከሉን እና ውድቅ ከተደረገ ለምን እንደተከለከለ ያሣያሉ።

ዋናው ደጋፊዎችን እና መራጮችን ለማሳመን የተለያዩ ቴክኒኮችን መጠቀም እንደ ማስታወቂያ፣ የመራጮች ዝርዝር መረጃ መያዝ፣ አባላትና ደጋፊዎችን ለቅስቀሳ ሥራ ማሰማራት የእጩዎችን የማሸነፍ እድላቸውን በእጅጉ ከፍ እንዲል ሊያደርግ ይችላል። ከፍተኛ

የዘመኑን የዲጅታል-ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ተጠቅሞ የቅስቀሳ ዘመቻን በማቀላጠፍ ደጋፊዎችን ከጎን ማሠለፍም ይቻላል፡፡ ቀጥለን ዋና ዋና የሚባሉት የምርጫ ቅስቀሳ ማሳመኛ መንገዶችን እንመለከታለን፡፡

## 2.6.1. በዲጅታል ቴክኖሎጂ የተደገፋ የምርጫ ቅስቀሳ

በመራጮች ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ ዲጅታል ቴክኖሎጂ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ አንዱ ዘዴ ድህረ ገፅን መሠረት ያደረገ ዲጅታል ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ የፖለቲካ ደጋፊዎችን እና መራጮችን ቁጥር ማብዛት ነው፡፡ ‹‹የምረጡኝ›› ቅስቀሳን የሚያከናውኑ ፖለቲከኞች ለመልዕክታቸው የሚራራላቸው መራጮችን ለማግኘት በኤሌክትሮኒክ እና በማህበራዊ ሚዲያ ግለሰቦች የሚደረጉ ግንኙነቶችን ለማግኘት የዘመኑን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡

የዘመቻ ስትራቴጂስቶች መራጮች በተወሰኑ ድረ-ገጾች ላይ ‹ክሊክ› ‹ሼር› እንዳደረጉ ለማወቅ በማገዝ በታለመላቸው የመራጮች ኮምፒውተሮች ላይ የፖለቲካ ማስታወቂዎችን መትከል ይችላሉ፡፡ የሚተላለፉ ጭብጥ የቅስቀሳ መልክቶች፤ ደጋፊዎች እና አባላት የላይክ ምልክት፤ የፌስቡክ ሼር ዘመቻ፤ የቲውተር ቲዊት ዘመቻ እንዲደረጉ ማበረታት አስፈላጊ ነው፡፡

***የቡድን መወያያ ጥያቄዎች***

1. *በዚህ የዲጅታል ዓለም ቴክኖሎ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ዓለም ውስጥ የመራጮችን የግል ምርጫ ለእጩ የፖለቲካ ትርፍ መጠቀሚያ ነው? ወይስ ምርጫን ለማሸነፍ አሳማኝ እና ተገቢ መንገድን መጠቀም ተገቢ ነው? ለምን?*

   *መልሱን በቡድን ተወያዩበት እና በጋራ ከአሠልጣኞችሁ ጋር ተወያዩበት፡፡*
2. *ከሴቶች እና ከወንዶች በዲጅታል ተክኖሎ ማን የተሻለ አጠቃቀም አለው? ለምን? ይህ ምን አይነት ተፅዕኖ አለው?*

## 2.6.2. የፊት-ለፊት የምርጫ ቅስቀሳ

መራጮችን ለማሰባሰብ ሁለተኛው መንገድ ግለሰባዊ፣ ተናጠላዊ ዘመቻ ነው፡፡ በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ቀና እና ተፅዕኖ ፋጣሪ ከሆኑ መራጮች ጋር ፊት ለፊት ግንኙነት እና ውይይት

ማደረግ ተገቢ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ በበጎ ፈቃደኞች በግል ከተመራጩ ጋር የተገናኙ መራጮች ካልተገናኙት ይልቅ የመምረጥ እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ የመምረጥ ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹ ሰዎችን እንደገና ደጋግሞ ማነጋገር በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ በመገኘት ያነጋገራቸውን ዕጩዎች የመምረጥ እድላቸውን እንዲጨምር ያደርገዋል (Green & Gerber, 2008) ፡፡

መራጮች ለአንድ እጩ ድምጽ ለመስጠት ያላቸውን ቁርጠኝነት ደጋግሞ ፊት ለፊት በማስታወስ፣ የምርጫ ቅስቀሳ  የፖለቲካ ፕሮግራም ሀሳቡን በንቃተ ህሊናቸው ውስጥ እንዲቀመጥ በማድረግ እና ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን በማክበር እና ሰዎች አመለካከታቸውን ወደ ተግባር እንዲቀይሩ ሊረዳቸው ይችላል፡፡ ይህ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታም አወንታዊ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ከዘመቻዎች አንፃር ሚዲያዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች ውስጥ ብቸኛ አማራጭ የሌላቸው ስልቶች እንዳልሆኑ ያስረዳናል፡፡  ከቤት ወደ ቤት የሚደረግ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ጉዳዮች እና ብዙ መራጮች ጠንካራ አመለካከቶች ስላላቸው እና በተቃዋሚዎች መልእክቶች በቀላሉ ተጽእኖ ስለማይኖራቸው በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ መልካም የሆነ የሰዎች ግንኙነት መራጮች ላይ አመለካከቶችን ወደ ተግባር እንዲተረጉም ያደርጋቸዋል፡፡

### 2.6.3. ትዕይንተ ገፅታ የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ (The Panoply of Political Persuasion)

ትዕይንተ ገፅታ የፖለቲካ ተግባቦት ከበርካታ የፖለቲካ ተግባቦት አይነቶች አንዱ ሲሆን ዕጩ ተወዳዳሪዎች እና የዕጩ ደጋፊዎች የመወዳደሪያ ምልክታቸውን፣ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን በህዝባዊ ጎዳናዎች እና አደባባዮች፣ የፖለቲካ መለያ ምልክታቸውን በልዩ ልዩ አልባሳት ላይ አርማቸውን በማሠራት፣ የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ፎቶ ለህዝብ ዕይታ በማቅረብ

ወዘተ....የመሳሠሉትን ህዝባዊ ዕይታ መንግዶች በመጠቀም የሚከወንና የመራጩን ህዝብ ትኩረትና ቀልብ ለማግኘት የሚደረግ ፖለቲካዊ ቅስቀሳ ስልት ነው፡፡ በገጠሩ አካባቢ እንደፈረስ እና በቅሎ ያሉ የጋማ ከብቶች፣ በከተማ አካባቢ ደግሞ እንደ ሞተር ሳይክልና ለዚህ ስራ በተዘጋጁ ክፍት የሆኑ መኪናዎች አማካኝነት ይከናወናል፡፡

የአንድን አካባቢ ህዝብ በአንድ በተወሰነ አደባባይ ወይም ስፍራ በመሰብሰብ የዛን አካባቢ የተለየ ታሪካዊ ገድል ወይም አካባቢ ታላላቅ ገድል የፈፀሙ ሰዎችን ወይም ተፈጥሯዊ ልዩ ሁኔታ በማድነቅ ከራስ የፖለቲካ ፍላጎት/አጀንዳ ጋር በማዛመድ የመራጩን ህዝብ ትኩረት ለማግኘት የሚደረግ የፖለቲካዊ ተግባቦት አይነት ነው፡፡

ነገር ግን የአንድን አካባቢ ሰው ሰራሽ ገድሎችም ሆነ ተፈጥሯዊ ልዩ ጉዳዩች ለመራጩ ህዝብ ስንናገር፣ በቃላት አጠቃቀማችንም ሆነ በንግግር ይዘቱ ላይ ሌሎች አካባቢዎችን ህዝቦች ቅሬታ እንዳያስነሳብን ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ እንደኛ በሃገር የታሪክና የአካባቢ ቁርሾዎች በበዙበት ሀገር ላይ ትዕይንተ ገፅታ የፖለቲካ ተግባቦት በምናደርግበት ወቅት የንግግርና የቃላት አመራረጣችን ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልን ግን ብዙ ፖለቲካዊ መዘዞችን ያመጣል፡፡

ቀጥሎ ከትዕይንተ ገፅታ የፖለቲካ ተግባቦት ጋር በተያያዘ አንድ ውስን ጥናት ቀርቧል፣ አንብቡትና ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡

### *ውስን ጥናት (Case Study)*

*ሳራ ፓሊን በነሀሴ 2008 በአሜሪካን በተካሄደው ምርጫ ሪፐብሊካን ምረጡኝ ቅስቀሳ በነበረበት ወቅት ሃገራዊና ብሄራዊ ትኩረት ከሳቡ ምርጥ ሴት ዕጩችዎች ግንባር ቀደም ናት፡፡ የፕሬዚዳንት እጩ ጆን ማኬይን ምክትል ፕሬዚዳንታዊ እጩ አድርጎ ሰየማት፡፡ ምክኒያቱም በምርጫ ቅስቀሳው የመጨረሻ ጭራ የነበረው ማኬይን በምረጡን ቅስቀሳ ወቅት የበለጠ ጉልበት*

ለመጨመር፣ የምክትል ፕሬዚዳንቱ እጩ እንደሚያስፈልገው በእጅጉ ያምን ነበር። ህዝባዊ ዘመቻውን ‹‹ሀ›› ብለው ለሁለት ጀመሩ። ፓሊን ገና የ44 ዓመቷ የአላስካ አካባቢ ገዥ ነበረች። እንከን የለሽ ወግ አጥባቂ እወነተኛ ምስክርነቶች እና አነቃቂ የህይወት ውጣወረዶች ታሪኳ ለመራጩ ህዝብ ፍቱን መድሃኒቱ ይመስሉ ነበር። እንደዚህ አይነት በህይወት ተሞክሮና ምስክሮች ለምርጫው ቅስቀሳ ዘመቻዎች እንደሚያስፈልጋት በፅኑ ታምን ነበር።

ፍቅረኛዋን ያገባች የውበት ንግስት ነበረችበትና ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረችበት ወቅት ነው። ሴትነትዋ ከፖለቲካ ተሳትፎና ዘመቻም አላገዳትም። አምስት ልጆችን ወለደች፣ አንድ ወንድ ልጅ ወደ ኢራቅ ለውትድርና እንደማንኛውም አሜሪካዊ ልካለች። ሶስት ሴት ልጆች እና አንድ የእድገት ውስንነት ያለበት ወንድ ልጅ አሳድጋለች።

ሳራ የፖለቲካ መሪነት ለወንዶች ብቻ የተሠጠ የሚመስለውን ጉዳይ እሷግን በእጅጉ ተማርካበት አለች። በአሜሪካ በአላስካ ትንሽ ከተማ ዋሲላ ለከተማ ምክር ቤት ተወዳድራ በርካታ ወንድ ዕጩዎች አሸንፋለች። ሁለት ጊዜ ከንቲባ ሆና በህዝብ ተመርጣለች። በ2006 የአላስካ የመጀመሪያዋ ሴት አስተዳዳሪ ሆና ተመረጠች። በዘይት አምራቾች ላይ የወሰደችው ፖለቲካዊ አስተዳደራዊ እርምጃ፣ ለዘይት ታክስ በተሳካ ሁኔታ በፖሊሲዋ የተዋጋችበት እና ለሃገረ መንግስት ግንባታ ሚውል 12 ቢሊዮን ዶላር ትርፍ ለህዝብ ማስገኘት ችላለች።

እሷ የራሷ የአቋም ሰው የሆነች በሳል ሴት፣ ከጥገኝነት የተላቀቀች በፖለቲካ አመራርና ቅስቀሳ ስልቷ የተለየች፣ ታታሪ ሴት በመሆኗ በብዙዎች ዘንድ አድናቆትን አትርፎላታል። ከዚህም በላይ የሪፐብሊካንን ደጋፊዎች እና መራጮች እያስደነቀች፣ አስገዳጅ የፖለቲካዊ እርምጃ የወሰደች፣ ንግግር አዋቂ፣ ጀግና ሴት መሆኗን በቅስቀሳ ስልቷ አሳይታለች።

የሳራ ፓሊን ገጽታ እና የምርጫ ቅስቀሳ ብቃትን ማሻሻል፣ የፖለቲካ ተግባቦት ብቃት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በዚህም የምርጫ ቅስቀሳ ብቃቷ እጅግ በጣም በርካታ አድናቂዎች እና ደጋፊዎችን ማፍራት ችላለች።

በመጨረሻ ግን በተሸረበው የፖለቲካ ድራማ ብዙም ሳይቆይ የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻዋ እየደበዘዘ መጣ። ምንም እንኳን የቤተሰብ አመራሯ እና ሃይማኖታዊ አቋሟ በብዙዎች አድናቂዎች ድጋፍ ያስገኛላት ቢሆንም፤ ሴት ልጇ ከጋብቻ በፊት ማርገዝን ተከትሎ፤ የመገናኛ

*ብዙኀን እና ፖለቲከኞች መነጋገሪያ ሥለነበር በምርጫ ቅስቀሳና ዘመቻ፣ በመራጮች ዘንድ ያገኙቸውን ተደማጭነትና ተቀባይነት ጥላሸት ቀባባት፡፡*

*ሳራ ፓሊን በአሜሪካ የሴት ፖለቲከኞች ውስጥ በምርጫ ቅስቀሳና ዘመቻ ስማቸው ከፍ ካሉ ጥቂት ሴት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወስጥ በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች፡፡ በ2008 እሷ እና ማኬይን በኦባማ ከተሸነፉ በኂላም ሳራ የፖለቲካ ቅስቀሳና ዘመቻ ንግግሯ በቴሌቭዥን ዜና ላይ በቂ የአየር ሰዓት ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጎ ነበር፡፡*

*ምንጭ፡ ከሪቻርድ ኤም ፔርሎፍ የፖለቲካ ተግባቦት ተለዋዋጭነት ገፅ 8 ለማሠልጠኛ መመሪያው በሚመች መልኩ የተወሰደ*

*የቡድን መወያያ ጥያቄዎች*

*ከላይ በቀረበው ውስን ጥናት መሠረት ቀጥሎ ያሉትን ጥያቂዎች በቡድን ተወያዩባቸው*

1. *ከሳራ ፓሊን የፖለቲካ አመራር እና የፖለቲካ ቅስቀሳ ስልት ምን ትማራላችሁ?*
2. *ከሳራ ፓሊን የፖለቲካ ውጣ ውረድ ምን ትገነዘባላችሁ?*
3. *እናንተ ሳራ ፓሊን አይነት የፖለቲካ ተግባቦት እና ስኬት ለመድረስ ምን ያስፈልጋችሃል?*
4. *እናንተ ሳራ ፓሊን አይነት መጨረሻ ላይ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ መቀዝቀዝና መደብዘዝ እንዳይገጥማችሁ ከእናንተ ምን ይጠበቃል?*

## 2.7. ሴቶች እና የፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ

***የቡድን መወያያ ጥያቄዎች***

1. *በሃገራችን ከተካሄዱ ስድስት ተከታታይ ምርጫዎች በመነሳት የሴቶች የምርጫ ቅስቀሳ ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር?*
2. *ሴቶች በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ምን ምን ተግዳሮቶች ሲገጥማቸው ተመለከታችሁ?*

የምርጫ ቅስቀሳ አደባባይ ወጥቶ በሕዝብ ፊት የሚደረግ የሴቶች በራስ መተማመንን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሴቶች ይህን አሟልተው በራስ መተማመን ይዘው ከበረቱ በፖለቲካና በህዝባዊ አመራርነት ከወንዶች ጋር እኩልነታቸውን ማስመስከር ይችላሉ፡፡ በርካታ የጥናት ውጤቶች እንደሚያመለክቱት በፖለቲካ የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ታማኝነታቸውን በመጠበቅ በመራጮች ዘንድ ተቀባይነት አላቸው፡፡

ከሴቶች የፖለቲካ የምርጫ ቅሰቀሳ ተሳትፎ ጋር ተያይዞ፣ አልፎ አልፎ የዲሞክራሲ ሥርዓት ባልዳበረባቸው ታዳጊ ሃገራት ውስጥ ከሚያጋጥሙ ችግሮች ውስጥ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የሚተላለፈውን መልዕክት ትተው በሴት እጩዎች መልክና አቋም ዙሪያ ሐሳብና አስተያየት የሚሰጡም ጥቂት አይደሉም፡፡ በተለይም በማኅበራዊ ድረ ገጾች በሚቀርቡ የሴቶች እጩዎች የምርጫ ቅስቀሳ ምስሎች ስር የሚሰጡ አስተያየቶች ለዚህ ማሳያ ሆነው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አለፍ ሲልም ሴቶች እጩዎች በቅስቀሳ ወቅት የፓርቲዎች ረዳትና አድማቂ እንጂ እጩ ተወዳዳሪ የማይመስሏቸው ሠዎች ቁጥር ጥቂት አይደሉም፡፡

በተጨማሪም ሴት ዕጩዎችን ከተመዘገቡ በኂላ ማስፈራሪያ እየተደረገባቸው ራሳቸውን ከዕጩነት እንዲያሰናብቱ የሚያደርጉ ሁኔታዎችም ቀላል አይደሉም፡፡ በእርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደ ሃገር የተወሰነ መሻሻል ቢኖርም እንኳን ለሴቶች ከሚፈለገውና ሊሆን ከሚገባው አንጻር እጅግ ብዙ እንደሚቀር መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ መሰናክል ከሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ የፓርቲዎች ድጋፍ አለመኖር፣ ለምሳሌ ለሴት እጩዎች የተገደበ የገንዘብ ድጋፍ መኖር፣ የፖለቲካ ግንኙነቶች መዳረሻዎችን መገደብ፣ በፖለቲካ ተቋማት ውስጥ ያለው የወንዶች የበላይነት፣ ወጣት ሴቶችን ወደ ፖለቲካ ህይወት ለመምራት በደንብ የዳበሩ የፖለቲካ ትምህርትና ሥልጠና ስርዓቶች አለመኖር እና ለወንዶች የሚጠቅመው የምርጫ ስርዓቶችን መዘርጋት ወዘተ….የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳታፊ እንዳይሆኑ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንዱ የፖለቲካ ሥርዓቱ ዴሞክራሴያዊ ባለመሆኑ እና መጠላለፍ የበዛበት ስለሆነ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ችግር መኖሩ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ፍላጎት እንዲያጡ እንዳደረጋቸው የጥናት ውጤቶች ያረጋግጣሉ፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች በሃገር ግንበታ ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና መጫወት ሲጀምሩ፣ ሴቶችን በዕጩነት ዝርዝራቸው ማስተዋወቅ፣ ለሴቶች እጩዎች ተገቢውን ስልጠና እና ድጋፍ መስጠት፣ ለምርጫ ቅስቀሳ የሃገር ሃብትን በፍትሃዊ እኩል መመደብ ወሳኝ ነው፡፡

በብዙ አገሮች የፓርቲ የስርዓተ ፆታ ኮታዎች በፈቃደኝነት ወይም በሕግ አውጭ መስፈርት ምክንያት መቀበል ባለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ በጣም ተቀባይነት ያለው እየሆነ መጥቷል፡፡ የሥርዓተ-ፆታ ኮታ አተገባበር ግን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሴቶችን በፖለቲካው ወደፊት ለማራመድ የሚጠቀሙበት ብቸኛ መንገድ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይልቁን የሴቶችን ፖለቲካዊ አመራርና ውሰኔ ሠጭነት የሚፈታተኑ ተያያዥ ማነቆዎች የሚታረሙበትና የሚወገዱበትን መንገድ በማስተካከል ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸውን እኩልነት የሚረጋገጥበትን ፖለቲካዊ ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ነው፡፡

በራስ መተማመን ያላቸው ብቁ እና ንቁ የሆኑ ሴት ፖለቲከኞች ወይም ተመራጮችን ለማፍራትና ስኬታማ የምርጫ ቅስቀሳም ለማድረግ ከኮታ ይልቅ፣ ፖለቲካዊ አቅም

ያላቸውን ሴቶች ወደ ህዝባዊ አመራር ማምጣት ላይ መስራት ተገቢ ነው። ይህም በሂደት የማኅበረሰቡን ዕይታ ስለሚለውጥ ሴቶችን በብዛትና በብቃት በፖለቲካው ላይ ለማሳተፍ ጥሩ የምርጫ ቅስቀሳ አቅም ያላቸውን ወደፊት ማምጣት ተገቢ ነው።

## ማጠቃለያ

የአካባቢዊና ሐገራዊ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች የመራጮችን ትኩረትና ይሁንታ ለማግኘት፤ ለማሳመን የሚደረጉ የጥረቶች ውጤት ናቸው። ማሳመን ማስገደድ አይደለም። መራጮችን ማሳመን የቃል ክርክር፣ ማስረጃ እና ስሜትን የሚስብ በተግባር የተፈተነ ልምድ የሚጠይቅ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

የማሳመን ንድፈ ሃሳቦች የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎችን ለመረዳት ፍኖተ ካርታ ያስፈልጋል። እጩዎች ሦስቱን የማሳመን ምሰሶዎች ማለትም ልምድ፣ ታማኝነት እና በጎ ፈቃድ አቅናጅቶ መጠቀም እንደሚያስፈልግ መረዳት ያሻል። የፖለቲካ አሳቢዎች ምሳሌያዊ ጭብጦችን በአንድ ላይ በማጣመር ታሪኮችን የሚናገሩ የትረካ መልዕክቶችን መጠቀም ጠቀሜታው ከፍ ያለ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

የመራጮች ተነሳሽነት እና አመለካከቶች በፖለቲካዊ የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ። እጩዎች የመራጮችን ተሳትፎ ደረጃዎች እና የአሰራር ስልቶችን ለማስማማት መልእክቶችን ለማበጀት ይሞክራሉ። በዝቅተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ባላቸው መራጮች የፖለቲካ መልእክቶች አጭር እና ቀላል መልዕክቶችን መጠቀም ውጤታማ ያደርጋል።

ሆኖም የመራጮች በጠንካራ ሁኔታ የያዙት አስተያየቶች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ የሚጫወቱትን ሚና አቅልለን ልንመለከተው አይገባም። ምክንያቱም መራጮች ባዶ ሰሌዳዎች አይደሉም። የማህበራዊ ዳኝነት ፅንሰ-ሀሳብ እንደሚያጎላው ከሆነ፤ መራጮች ከአድሎአዊነታቸው ጋር በተዛመደ መረጃን መርጠው ይገነዘባሉ። እጩዎች የሚያነሷቸውን ሃሳቦች በጥንቃቄና በሚዛኑ መመልከት አለባቸው። እጩዎች ስለማህበራዊ ጉዳዮች ግልጽ ያልሆኑ መግለጫዎችን ከሰጡ ወይም አንድ የመራጮች ክፍል የሚቃወመውን ነገር ቢናገሩ፤

የመራጮችን ልብ የሚነካ አቋም እንደ ተቃዋሚ ሊገነዘቡ ይችላሉ። አንዳንድ መራጮች በእነዚህ ምክንያቶች እጩውን ውድቅ ሊያደርጉ ይችላሉ። ምክንያቱም በፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ ውስጥ መራጮች ሁል ጊዜ ሙሉ በሙሉ ምክንያታዊ ወይም ፍትሃዊ እንደሆኑ ማሰብም ተገቢ አይደሉም።

በዚህ በዘመነ ዲጅታል ቴክኖለጅ ዓለም ውስጥ የመራጮችን ስሜት የሚቀሰቅሱ ጉዳዮችን በደህረ ገፅ ሲለቀቁ፣ እጩዎች የስነ ምግባር እና የፖለቲካ ቀውስ ያጋጥማቸዋል። በመርህ ላይ የተመሰረተ አቋም ከያዙ ለሀሳቦቻቸው እውነት ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን ተቃራኒው ደግሞ የምርጫ ቡድኖችን ሊያራርቋቸው ይችላል። ለሚያምኑት ነገር ጥብቅና ሳለመቆም በመምረጣቸው ከመርህ ውጪ እየሰሩ ናቸው የሚለውን አባባል ስማቸውን ያጎድፏል። በተለይ ደግሞ አላግባብ ስም መጠፋፋቱ ሂደት ውስጥ ሴት ፖለቲከኞች ብዙውን ጊዜ ተጠቂ ናቸው። እንግዲህ ፖለቲካ እንዲህ ነው። ፖለቲከኞች ምክንያታቸውን በጥበብ መምረጥና መምራት አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ እጩዎች ሆን ብለው ከፋፋይ ጉዳዮችን ለማንሳት ይመርጣሉ። አሳማኝ በሆኑ መራጮች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ይሞክራሉ።

ነገር ግን የፖለቲካ የምርጫ ዘመቻዎች የሞራል ፍልስፍና ልምምድ እንዳልሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል። አንዳንዳንድ ጊዜ ማሳመን ከእውነት ጋር የማይመሳሠልበት አጋጣሚ ብዙ ነው። እጩዎች ለተለያዩ ድምጽ ስጭ ቡድኖች ድምፅ ሥጡን በማለት ልዩ ልዩ መደለያዎችን ይዘረጋሉ። ከተለያዩ አካላት ጋር ጉዳዮችን በተለየ መንገድ ያዘጋጃሉ። በመጨረሻው የሀገራዊ ምርጫ ዘመቻዎች ህዝቡ ስለ ውስብስብ የፖሊሲ ችግሮች እንዲያስብ ወይም መራጮች የአገሪቱን የፖለቲካ ውዝግቦች ለመፍታት የተለያዩ አመለካከቶችን ማድነቅ እንደሚያስፈልግ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የተነደፉ አይደሉም። ምክንያቱም ፖለቲከኞች ጉዳዮችን ከራሳቸው ዕይታና ፍላጎት ስለሚያስረዱ ነው።

# ክፍል ሦስት

## 3. የኢትዮጵያ ምርጫ ቅስቃሳ ዘመቻ ህጋዊ ማዕቀፎች

### መግቢያ፡

በዚህ ክፍል ከፖለቲካ ‹የምረጡኝ› ቅስቀሳ ዘመቻ ጋር በተያያዘ ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ማድረግ እና ማድርግ የሌለባቸውን ጉዳዩች ከህጋዊ ማዕቀፎች አኳያ እንመለከታለን፡፡ የምርጫ ቅስቀሳ ህጎችን ማወቅ ለውጤታማና ህጋዊ የፖለቲካ ተሳትፎ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ከፖለቲካዊ ተግባቦት ጋር ተያይዞ ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ የቋንቋ ይዘት አጠቃቀም እንመለከታለን፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ህጎችን መተላለፍ ወይም አለማወቅ (Ignorance of the Law) ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ሴት ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት የሚፈጠሩ ስህተቶችን ቀድሞ አውቆ ለማረምና ውጤታማ ለመሆን፤ ከህግ ጥህተቶች የፀዳ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ለማከናወን ያመች ዘንድ እነዚህን ህጋዊ ማዕቀፎች በዚህ የስልጠና መመሪያ ማካተት አስፋለጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ዋና ዋና አላማዎች**

**ሰልጣኞች ይህንን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ ቡኋላ፡-**

- ሴት ዕጩዎች/የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ሂደት ማደረግና ማድረግ የሌለባቸውን ህጋዊ ፍሬ ጉዳዩች ይገነዘባሉ፤
- መራጮች በምርጫ ዘመቻው ወቅት ሊኖራቸው የሚችሉ ዋና ዋና መብቶች ያውቃሉ፤
- ከፖለቲካዊ ተግባቦት ጋር ተያይዞ ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ ይዘት አጠቃቀሞችን ያውቃሉ፤
- በምርጫ ውድድር፤ ፖለቲካዊ የቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴ ህጋዊ ክልከላዎች የተጣለባቸውን ጉዳዩች ይገነዘባሉ፤

## 3.1. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ አካሄድ (Rules of Election Campaign)

*የቡድን መወያያ ጥያቂዎች*

*ወድ ሠልጠኞች!*

1. *እናንተ ከዚህ በፊት ባላቹህ ቅድመ እውቀት የፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች በፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ማድረግ ያለባቸውን አንድ በአንድ እየዘረዘራችሁ ተወያዩባቸው?*
2. *እናንተ ከዚህ በፊት ባላቹህ ቅድመ እውቀት የፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች በፖለተካ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ማድርግ የሌለባቸውን ጉዳዮች ተወያዩባቸው?*
3. *በመጨረሻም አሰልጣኛችሁ በሚሠጢችሁ የሚና ጨዋታ(Role play) የተወሰናችህ ሠልጣኞች እንደ ህዝብ፣ የተወሰናችህ ደግሞ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ/ዕጩ፣ ሌሎቻችሁ ደግሞ እንደሚዲያ ባለሞያ ሁናችህ ህጋዊ የፖለቲካ ቅስቀሳ ዘመቻን አሳዩ:: ከዛም ስህተቶች ካሉ ተራረሙ::*

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1162/2019 አንቀፅ 129 የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ በሚካሄድብት (Rules of Election Campaign) ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች ማድረግ ያለባቸውን በግልፅ በድንጋጊው አሰቀምጧል:: በዚህ መሠረት ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ/ዕጩ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ፣ የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለ ስጋት የማሰራጨት፣ መብቶቻቸውን የማክበር፤ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ በሚካሄድብት ወቅት እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጩን ሕዝብ እና የሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ያከበረ መሆን እንዳለበት፤ የመገናኛ ብዙኃን ነፃነትን ማክበር፤ ተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ማክበር፤ በፖለቲካ እንቅስቃሴ

ለመሳተፍ የሚሹ የመምረጥና የመመረጥ መብት ያላቸው ዜጎች ሁሉ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ እንዳለበት ህጉ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡

በተጨማሪ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ/ዕጩ የግል ወይም የመንግሥት ጋዜጠኞች በሙያዊ ስራቸው ላይ እንዳይሰማሩ ማዋከብ፣ እንቅፋት መፍጠር፤ በማንኛውም አይነት ድርጊት የሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጐል፣ እንዲቋረጥ፣ እንዲበላሽ፣ እንዲዳከም ማድረግና ብሎም መተባበር፤ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ መከልከል እንደሌለበት እና ይህንን ያደረገ ህጋዊ ቅጣት ሊጠብቀው እንደሚችል ህጉ ያስቀምጣል፡፡

በተጨማሪም የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ፖስተሮችን ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ እንዳይታዩ ወይም እንዳይነበቡ ማድረግ፤ ወይም ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ የእግር ጉዞ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርግ በአመራሩ፣ በአባላቱ፣ ወይም በደጋፊዎቹ አማካኝነት ማገድ፣ ማወክ፣ ቅስቀሳ ማድረግ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ማደናቀፍ እንደሌለበት በግልፅ ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ እንዳይሳተፍ መከልከል፤ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈፅሙ መቀስቀስና ማነሳሳት የለበትም በማለት ይደነግጋል፡፡

በተጨማሪም አዋጅ ቁጥር 1162/2019 አንቀፅ 127 ንዑስ አንድ እንደሚያብራራው በመድብለ ፓርቲ በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚመረጥ መንግሥት ህጋዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ሊመሰረት እንደሚችል ያስረዳል፡-

1. መራጮች በምርጫ ዘመቻው አማካኝነት ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲዎችና ስለ እጩዎች ማንነት የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና የራሳቸውን በእውቀት ላይ በተመሰረተ እና ከግል ፍላጎት የሚመነጭ ውሳኔ ሲያደርጉ፤
2. መራጮች በነፃነት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለፍርሃት፣ ያለተፅእኖ፣ ያለጫና፣ እንዲሁም ከጉቦ እና ከተለያዩ መደለያዎች ነፃ በሆነ መልኩ ድምፅ መስጠት፤ ሲችሉ ብቻ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሊከናወን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

## 3.2. ለምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ የተከለከሉ ሥፍራዎች

*የቡድን መወያያ ጥያቄዎች*

*ወድ ሠልጠኞች!*

1. *እናንተ ከዚህ በፊት ባላችሁ ቅድመ እውቀት የፖለቲካ ፓርቲዎች/ዕጩዎች በፖለተካ ቅስቀሳ ዘመቻ በማንኛው ቦታና ሥፍራ ማካሂድ ይችላልን? ለምን ምክኒያቱስ? የትኞቹ ቦታዎችና ስፍራዎች?*
2. *በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ከፖለቲካዊ ተግባቦት ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸውን ጉዳዩች አብራሩ?*

የሃገራችን የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2019 አንቀፅ 46 የምርጫ ውድድር የቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴ የተከለከለባቸው ቦታዎች በግልፅ አስቀምጧል፡፡ እነዚህም በሚከተሉት ቦታዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ ወይም ዘመቻ ማድረግ የተከለከለ መሆኑን ያብራራል፡፡ የእምነት ቦታዎች ማለትም ቤተ ክርስትያኖችና መስጊዶች፣ ወታደራዊ ካምፖች እና ፖሊስ ጣቢያዎች፤ የመማር ማስተማር ሂደት ተግባር እየተከናወነ በሚገኝበት ወቅት በትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ቤቶች አካባቢ በ200 መቶ ሜትር ርቀት ዙሪያ፤ ህዝብ የዕለት ተለት ግብይት በሚፈፅምባቸው እና በተወሰኑ ቀናት በገጠርም ሆነ በከተማ በይፋ ገበያ እየተካሄደ በሚገኝባቸው ቦታዎች በ200 ክልል መቶ ሜትር ዙሪያ፤ የመንግሥት ወይም የህዝብ መደበኛ ሥራ በመከናወን ላይ የሚገኙባቸው የመንግሥትና የህዝብ ተቋማት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት መደበኛ የሥራ ሰዓት እና ቦታ፣ ሌላ ህዝባዊ ስብሰባ እየተካሄደ ባለባቸው ቦታዎች እና አካባቢዎች ህዝባዊ የፖለቲካ ቅስቀሳና ዘመቻ ማድረግ የተከለከለ መሆኑን አዋጁ በግልፅ ያብራራል፡፡

በተጨማሪም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 132 ከፖለቲካዊ ተግባቦት ጋር ተያይዞ ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ ይዘት እና ሰላማዊነት ህጉ እንደሚከተለው ያስገነዝባል፡፡ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የምረጡኝ ዘመቻውን ሲያደራጅና ሲያካሂድ ለአጠቃላይ የምረጡኝ

ዘመቻ፣ ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራ እና ለድህረ ምርጫ ሂደቱ ሰላማዊነትና ስኬት አስተዋፅኦ በሚያደርግ አኳኋን ማድረግ አለበት፡፡ ከሚጣልበት ኃላፊነትና ካለው ክብር ጋር በተመጣጠነ ደረጃ መንቀሳቀስ አለበት፡፡ ማንኛውም ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ንግግር የሚያደርግ ዕጩ/የፖለቲካ ፓርቲ ወኪል፡-

- ግጭት ቀስቃሽ የሆነ ወይም የግል ስብዕናን የሚነካ ቋንቋ ማስወገድ አለበት፤
- በማንኛውም መልኩ ለአመጽ የሚጋብዝና በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ስጋትን የሚጭር የቋንቋ አጠቃቀም ማስወገድ እንዳለበት ያሥረዳል፡፡
- ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በይፋም ሆነ በስውር አመፅ የሚቀሰቅስ ወይም በማንኛቸውም የመገናኛ ብዙሃን የሚያበረታታ የቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔት ወይም ፖስተር ማሳተም ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

## 3.3. በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሥለሚኖር ህጋዊ መስተጋብር

*የቡድን መወያያ ጥያቄዎች*

*ውድ ሠልጣኞች!*

1. *ሃገራችን ኢትዮጵያ እስካሁን ስድስት ተከታታይ ምርጫዎችን አካሂዳለች፡፡ ታዲያ እስካሁን ካለፉት ምርጫዎች በፓርቲዎች/በዕጩዎች መካከል በምረጡኝ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ምን ዓይነት መስተጋብር በፓርቲዎች መካከል ታዘባችሁ? በመልካም ምን ተመለከታችሁ?*
2. *ለዲሞክራሲ ሥርዓት እና ለህግ የበላይነት እንቅፋት የሆኑ መስተካከል ያለባቸው አሉታዊ ጉዳዩችስ?*

የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ አንቀፅ 146 ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ ማለትም የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ እንደለለበት እና ይህንን ፈፅሞ የተገኘ በግልፅ የስነ ምግባር ጥሠት እንደፈፀም ተቆጥሮ ህጋዊ ቅጣት እንደሚጠብቀው ያስረዳል፡፡

እንዲሁም ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በዕጩነት እንዳይመለምልና ጽህፈት ቤት እንዳይከፍት በማናቸውም መንገድ ያደናቀፈ ወይም የተከፈቱ ጽህፈት ቤቶች በነፃነት እንዳይሠራባቸው በግልፅም ሆነ በስውር ያወከ ወይም ሁከት እንዲፈጠር ያደረገ ወይም በማንኛውም ዓይነት ድርጊት የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ እና ፓርቲዎች ያዘጋጁት የድርጅት ልሳን፣ የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ፣ እንዳይታይ ወይም እንዲበላሽ ያደረገ ወይም እንዳይለጠፍ ያወከ ወይም የተለጠፈውን የቀደደ፣ ያበላሸ፣ ያነሳ፣ ያጠፋ፣ የሌላን የፖለቲካ ፓርቲ ምልክት ወይም አርማ የቀዳ ወይም አስመስሎ የተጠቀመ፣የሌላ ፖለቲካ ፓርቲን የምርጫ ቁሳቁስ የሰረቀ ወይም ያበላሸ ወይም ያጠፋ አንደሆነ፤ የሥነ ምግባር ጥሰት እንደፈፀመ ይቆጠራል በማለት ይደነግጋል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

በዲሞክረሲ ሥራዓት ማንኛውም የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ ዓለም አቀፍ የምርጫ መርሆዎችን አካትቶ በያዘ ህግ እንዲመራ ማድረግ ለህጋዊና ሠላማዊ ምርጫ ስኬት ጠቀሜታው የጉላ ነው፡፡ በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት ዕጩዎች ማድረግ እና ማድርግ የሌለባቸውን ጉዳዩች ከህጋዊ ማዕቀፎች አኳያ መገንዘብ፣ ከፖለቲካዊ ተግባቦት ጋር ተያይዞ ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ እና ስለማይሉ የቋንቋ ይዘት አጠቃቀሞች ግልፅ መረጃ መያዝ፣በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ወቅት የሚፈጠሩ ስህተቶችን ቀድሞ አውቆ ለማረምና ውጤታማ ለመሆን የምርጫ ሥነ ምግባር ህጉን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

የፖለቲካ ፓርቲ/ዕጩ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ፣ የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለ ስጋት የማሰራጨት፣ መብቶቻቸውን የማክበር፤ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ በሚካሂድብት ወቅት እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጨን ሕዝብ እና የሌሎች የኀብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ያከበረ መሆን እንዳለበት፤ የእምነት ቦታዎች ማለትም ቤተ ክርስትያኖችና መስጊዶች፣ ወታደራዊ ካምፖች እና ፖሊስ ጣቢያዎች፤የምረጡኝ ቅስቀሳ ወይም ዘመቻ ማድረግ የተከለከለ መሆኑን፣ ከፖለቲካዊ ተግባቦት ጋር ተያይዞ ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ እና ይዘት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያሥፈልግ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

# 4. ዋቢ መፀሐፍት (Referance Book)

Bilandzic, H., & Busselle, R. (2013). Narrative persuasion, In J.P. Dillard & L. Shen (Eds.), The Sage handbook of persuasion: Developments in theory and practice (2nd ed., pp. 200–219). Thousand Oaks, CA: Sage.

Chris Rose, (2005). How to Win Campaigns: 100 Steps to Success, published by Earthscan in the UK and USA.

Cohen, G.L. (2003). Party over policy: The dominating impact of group influence on political beliefs. Journal of Personality and Social Psychology, 85, 808–822.

David M. Farrell, 1992. Conclusion: The Contemporary Election Campaign, Electoral Strategies and Political Marketing. Houndsmills, UK: Macmillan Press, pp. 223–5.

Farrell, DavidM. 1996. Campaign Strategies and Tactics. In Lawrence LeDuc, RichardG. Niemi, and Pippa Norris, eds. Comparing Democracies. Elections and Voting in Global Perspective. Thousand Oaks, CA: Sage, pp. 160–83.

Green, D.P., & Gerber, A.S. (2008). Get out the vote. How to increase voter turnout (2nd ed.). Washington, D.C.: Brookings Institution Press.

Johnson, D.W. (2000). The business of political consulting, In J.A. Thurber & C.J. Nelson (Eds.), Campaign warriors: The role of political consultants in elections (pp. 37–52). Washington, D.C.: Brookings Institution Press.

Marshall Soules, 2015. Media, Persuasion and Propaganda, Edinburgh University Press Ltd.

McCroskey, J.C., & Teven, J.J. (1999). Goodwill: A reexamination of the construct and its measurement. Communication Monographs, 66, 90–103.

Richard M. Perloff, (2014). The Dynamics of Political Communication, Routledge publisher New York.

Schwartz, T. (1974), The Responsive Chord, New York: Anchor Books፤ Self-Determination Theory website, www.selfdeterminationtheory.org/.

West, D.M. (2014). Air wars: Television advertising and social media in election campaigns 1952–2012 (6th ed.). Washington, D.C.: CQ Press.

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ, (2019). የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅአዋጅ ቁጥር 1162/2019 .

በሐሚልተን አብዱልአዚዝ (2021). ፖለቲካዊ ሥነ ተግባቦት ጥቅምት 17/2012

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ (1995). የኢፌድሪ ህገመንግስት 1995.

Design & Printed by
Eldel Printing +251 960 43 73 53
eldelprinting@gmail.com

**በዚህ ያግኙን ፡**

:timranethiopia@gmail.com
http://www.timran-et.org
: @timran2012
: t.me/TIMRAN
: @timranethiopia